ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 178 የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

# የኢትዮጵያንና የፓኪስታንን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ኢንቨስተሮችን መደገፍ ያስፈልጋል

**በሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያንና የፓኪስታንን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ኢንቨስተሮችንና የቢዝነስ ማኅበረሰቡን መደገፍ አስፈላጊ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ለቀጣይ አምስት ቀናት በሚቆየው የውይይት መድረክ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን፤ የፓኪስታን ኢንቨስተሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ለማልማት ፍላጎት በማሳየታቸው አመስግነዋል። የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በጣም እየተጠናከረ ለመምጣቱ ማሳያ መሆኑንም ገልጸዋል። በኢትዮጵያ በኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ የውጭ ባለሀብቶች መንግሥት ምቹ የሆነ የኢንቨስትመንት ሁኔታን ለመፍጠር እየሠራ መሆኑን አክለው ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ የዕድገት ጉዞ በለውጥ ጎዳና እንደሚገኝ የገለጹት አቶ ደመቀ፤ የኢትዮጵያንና የፓኪስታንን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር የሁለቱ ሀገራት አምባሳደሮችና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል። ኢንቨስተሮችንና የቢዝነስ ማኅበረሰቡን መደገፍ በጣም አስፈላጊ ነው ያሉ ሲሆን ከዚህ ውይይት በኋላ የተለያዩ የልማት ቦታዎችንና የኢንዱስትሪ ፓርኮችን እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበዋል።

ኢትዮጵያ የአስር ዓመት ሀገር በቀል የልማት ዕቅድ ይዛ ድህነትን ለመቀነስ እየሠራች ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህም መሠረት የሀገሪቷ የኢኮኖሚ

የኢትዮጵያንና የፓኪስታንን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ - ዳኜ አበራ

አቶ ደመቀ መኮንን

# ሁሉን አቀፍ የሽግግር ፍትሕ እርቅን ለመፍጠር ወሳኝነት እንዳለው ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ሁሉን አቀፍ የሽግግር ፍትሕ ሂደት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በሕጋዊ መንገድ መፍትሔ በመስጠት እርቅን ለመፍጠር ወሳኝነት እንዳለው ተገለጸ።

ሁሉን አቀፍ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሽረ

**ጌትነት ምህረቴ**

ሽረ፡- ተሳፋሪው ወደ አውቶብስ መናኸሪያ እየተጣደፈ ይገባል፤ ተሽከርካሪዎች ተሳፋሪዎችን ይዘው፤ ይወጣሉ፣ ይገባሉ። ተራ አስከባሪዎች የሕዝብ ትራንስፖርት ሰጪ ተሽከርካሪዎችን ሥርዓት ሲያሲዙ ይታያል። ሕይወት በመናኸሪያ ሩጫ ናት። የሰው ግርግር፣ተሽከርካሪዎች ተሳፋሪን ጭኖ ለመውጣት የሚያደርጉት ጥድፊያ የትራንስፖርት እንቅስቃሴው ወደ መደበኛ ተግባሩ እየተመለሰ መሄዱን ያረጋግጣል።

መቐለ፣አክሱም፣ዓድዋ፣ሽራሮ፣አዲግራት፣ውቅሮ..... እያሉ የሚጠሩ ረዳቶች ተሳፋሪን ጭኖ ከመናኸሪያ ለመውጣት ይቻኮላሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው ተሳፋሪ አቶ ብርሃነ ገብረመስቀልን፤ ሽረ አውቶብስ መናኸሪያ

የሕዝብ ትራንስፖርት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ - እዮብ ተፈራ

# ለዓባይ ግድብ ባለፉት 7 ወራት ከ949 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ለዓባይ ግድብ ግንባታ ባለፉት ሰባት ወራት ከ949 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን የግድቡ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

ለዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







ዜና



አቶ ደበበ ዘውዴ

# ለ21 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ እየቀረበ ነው

**ማርቆስ በላይ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ድርቅን ጨምሮ በተፈጥሯዊ እና በሰው ሰራሽ ችግሮች ለተጎዱ 21 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ እየቀረበ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ።

የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ደበበ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት በተለያዩ ችግሮች ለተጎዱ ዜጎች የበኩሉን በማድረግ ላይ ነው። ድርቅን ጨምሮ በሰው ሠራሽ ችግሮች የተጎዱ ዜጎችን ለመርዳት ኅብረተሰቡ ድጋፍ በማሰባሰብ ሊረባረብ ይገባል።

እንደ አቶ ደበበ ገለጻ፤ ግለሰቦች፣ የበጎ ፍቃድ ማኅበራት እንዲሁም በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ በማስተባበር በተለያየ መልኩ መደጋገፍ የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ለተጎዱ 21 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዜጎች ድጋፍ እየቀረበ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ ይህም በትግራይ፣አማራ እና አፋር ክልሎች ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚገኙ 8 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎችን ያካትታል ብለዋል።

በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሚከሰቱ ችግሮች ለችግር የተጋለጡ ዜጎችን ለመደገፍ መንግሥት፣የዓለም ምግብ ፕሮግራም እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመሳተፍ ላይ መሆናቸውንም አስረድተዋል።

በቦረና በደረሰው ድርቅም ባለፉት ሁለት ወራት 204 ሺህ 756 ኩንታል ምግብ ማቅረብ መቻሉን ገልጸዋል።

ተጋላጭ ለሆኑ ሕጻናት፣ ነፍሰጡሮች፣አጥቢ እናቶች እንዲሁም አቅመ ደካሞች የኢትዮጵያ መንግሥት አስር ኩንታል አልሚ ምግብ በአስራ ሦስት ወረዳዎች ላይ እንዲዳረስ መደረጉን አስረድተዋል።

በድጋፉ በትግራይ፣ በአፋር እና አማራ 29 አጋር አካላት እየተሳተፉ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ደበበ መንግሥት ሰብዓዊ ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ጋር ግንኙነት በማድረግ ላይ ነው ብለዋል።

የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ከፍተኛ አደጋ በሚደርስባቸው ቦታዎች ላይ የአስቸኳይ ጊዜ ማስተባበሪያ ማዕከል በክልል እንዲሁም በዞን ደረጃ በማቋቋም መረጃ እንዲደራጅ በማድረግ ላይ ሲሆን ከዚህም ጋር ተያይዞ ያቤሎ ላይ የአስቸኳይ ጊዜ ማስተባበሪያ መቋቋሙን ገልጸው ይህም በክልሉ የሚመራና ሁሉንም ሴክተር ያካተተ ነው ብለዋል።

ማዕከላቱ መረጃ በማደራጀት እና የሚመጡትን የተለያዩ ሀብቶች ለብክነት ሳይዳረጉ ተደራሽ ለማድረግ ታሳቢ በማድረግ የተቋቋሙ መሆናቸውን አቶ ደበበ ገልጸዋል።

# በተፋሰስ ልማት ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በተያዘው ዓመት ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በተፋሰስ ልማት ለማልማት ታቅዶ እየተሠራ ነው ሲል የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፤በዚህ ዓመት ከ30 ሺህ በላይ በሚሆኑ ተፋሰሶች ላይ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ለማልማት ታቅዷል። ከጥር አጋማሽ ጀምሮ እስከ አሁን ባለው ጊዜ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት በተፋሰስ ልማት ለምቷል።፡

ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እያስገኘ ያለው የተፋሰስ ልማት ሥራ በ2015 ዓ.ም ማኅበረሰቡን ያማከለ በመሆኑ በተያዘለት ዕቅድ በሁሉም ክልሎች በስፋት እና በተነሳሽነት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም የተሠሩ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ 500 ሺህ ሄክታር መሬት የእድሳት እና የጥገና ሥራዎች የሚካሄዱ ይሆናል። እድሳቱ የሚደረገውም ባለፉት ዓመታት የእርከን ሥራ የተሠሩባቸው ቦታዎች በጎርፍ እና በተለያዩ ምክንያቶች ሊበላሹ በመቻላቸው ነው፤ ይህ ደግሞ የታችኛውን የተፋሰስ ማሳዎች ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል አዲስ እርከኖችን መሥራት እና ደረጃዎችን ማሳደግ ላይ የሚሠራ ይሆናል። ይህም በዚህ ዓመት ልንሠራው ያቀድነውን የተፋሰስ ልማት ሥራ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር ያደርሰዋል ብለዋል።

በተጨማሪም ከእንስሳትና ከሰው ንክኪ ነጻ በሆነ መልኩ 200 ሺህ ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል። ይህም ለአካባቢ ልማት ፤ ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ምንጮች እንዲጎለብቱ እንዲሁም የአፈር ለምነትን ለማስጠበቅና ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ሲሉ ሚኒስትር ዴዔታው ተናግረዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በድርቅ እና በጎርፍ ለሚነሱ ተፈጥሯዊ አደጋዎች ስትጋለጥ ቆይታለች ያሉት



ፕሮፌሰር እያሱ ኤልያስ

ሚኒስትር ዴዔታው ይህ ደግሞ የሚሆነው ከተፈጥሮ ሀብት መመናመን ፣ከአፈር መሸርሸር እና ከአካባቢ መራቆት ጋር በተያያዘ ነው። ይህን ለመቀልበስ እና አደጋውን ለመከላከልም ኅብረተሰቡን ባካተተ መልኩ ተፋሰሶች የሚለሙበት የመንግሥት አቅጣጫ ተቀምጦ እየሠራን እንገኛለን ብለዋል። ባለፉት ዓመታት የተሠሩ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ትልቅ ለውጥ ማምጣት መቻላቸውን ፕሮፌሰር እያሱ ጠቁመዋል።

# የኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞችን ቁጥር ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለማድረስ እየተሠራ ነው

**ሄርሞን ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በ2022 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት እንደሚዘረጋና የኤሌክትሪክ አገልግሎት ደንበኞችን ቁጥር ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለማድረስ እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ከቁልፍና ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ባደረገው ውይይት የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ሽፈራው ተሊላ እንደገለፁት፤ ተቋሙ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ እንደሚገኝና የደንበኞችን ፍላጎት በማርካት ተወዳዳሪ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት ሰፋፊ የለውጥ ሥራዎችን ተግባራዊ እያደረገ ነው። የስርጭት መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋትና በማዘመን ደንበኛ ተኮር አገልግሎት በመስጠት አስተማማኝ የፋይናንስ አቅም በመገንባት ወደ ትግበራ ይገባል። በ2022 ዓ.ም በመላ ሀገሪቱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ይዘረጋል ብለዋል።

ተቋሙ ከዚህ ቀደም አዘጋጅቶ በትግበራ ሂደት ላይ የሚገኘውን የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታና የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ መነሻ በማድረግ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችና ቀጣይ ተልዕኮዎችን ታሳቢ በማድረግ ይህንኑ በላቀ ደረጃ በማጎልበት ለሦስት ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ በመንደፍ የትኩረት አቅጣጫና ግቦች ተለይተው ወደ ሥራ እንደተገባ አቶ ሽፈራው ገልፀዋል።

ተቋሙ አራት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ደንበኞች እንዳሉት የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈፃሚው በቀጣይ ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለማድረስ እንደሚሠራም



አቶ ሽፈራው ተሊሳ

አብራርተዋል። የተያዘውን እቅድ ስኬታማ ለማድረግ 12 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስፈልገው የተናገሩት አቶ ሽፈራው ወደ ሥራ ለመግባት እንቅስቃሴ እየተደረገ ስለመሆኑ አስታውቀዋል።

በ2022 ዓ.ም ሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት እንዲያገኙ ራዕይ አድርጎ እየሠራ እንደሚገኝ የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈፃሚው፤ ለዚህ ዕቅድ ተግዳሮት የሆኑት ምክንያቶችም በዝርዝር ያስቀመጡ ሲሆን የሕዝቡ አኗኗርና የመልክዓ ምድር አሰፋፈር፣ የመሠረተ ልማቶች እርጅና፣ የፋይናንስ አቅም መገደብና የደንበኛ ቁጥር አነስተኛ መሆን ዋነኛ ችግሮች ናቸው ብለዋል።

ዜና

# ከ1.2 ሚሊዮን በላይ ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያን የማጓጓዝ ሥራ ተጀምሯል

## - እስካሁን 388ሺ. 206 ሜትሪክ ቶን ተጓጉዟል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ለ2015/16 የምርት ዘመን 1,287,500 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ለማጓጓዝ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ውል ገብቶ ሥራ መጀመሩን የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት አስታወቀ። እስካሁን ጅቡቲ ወደብ ከደረሰው የአፈር ማዳበሪያ 388ሺ. 206 ሜትሪክ ቶን መጓጓዙም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት (ኢባትሎአድ) ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚና የጭነት አስተላላፊ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሲራጅ አብዱላሂ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ ለቀጣዩ የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ ለማጓጓዝ ድርጅቱ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ውል ገብቷል።

ድርጅቱ በገባው ውል መሠረትም አንድ ሚሊዮን 287 ሺህ 500 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ግዢ ከሚፈፀምባቸው ሀገራት እስከ ሀገር ውስጥ መዳረሻ ስፍራዎች የማጓጓዝ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ አቶ ሲራጅ ገልፀዋል ።

ውል ከተገባበት ታኅሣሥ ወር 2015 ዓ.ም ጀምሮ እስካሁን 388 ሺህ 206 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ተጓጉዟል። አሁን ላይ ጅቡቲ ወደብ የተቀመጠው 9880 ሜትሪክ ቶን ብቻ ነው።

አጠቃላይ አንድ ሚሊዮን 287 ሺህ 500 ሜትሪክ ቶን የአፈር ማዳበሪያ ከታኅሣሥ መጀመሪያ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2015 ዓ.ም ድረስ አጓጉዘን ለማጠናቀቅ በእኛ በኩል እየሠራን ነው ያሉት አቶ ሲራጅ፤ የማጓጓዝ ሥራው በወቅቱ ሊጠናቀቅ የሚችለው የግዢ ሂደቱ በጊዜው ከተጠናቀቀ እንደሆነም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሲራጅ ገለፃ፤ ለማጓጓዝ ውል የተገባላቸው የአፈር ማዳበሪያዎች ኤል ፒ ኤስና ዩሪያ ናቸው።

የጭነት አገልግሎት ላይ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲነጻጸር መቀነስ ተስተውሏል። ይህ ሊሆን የቻለው በዋናነት የራሺያና የዩክሬን ጦርነት መከሰት፣ የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ፣ ዓለምአቀፉ የኮቪድ-19 መከሰት፣ የባንኮች ኤልሲ በብዛት አለመከፈትና ዓለማቀፍ የንግድ እንቅስቃሴው በመቀዛቀዙ መሆኑንም ተናግረዋል።

አሁን ላይ በብዙ መልኩ ችግሮቹ እየተቀረፉና እየተሻሻሉ ነው፤ ባንኮችም ኤልሲ የመፍቀድ ሁኔታ እየተስተዋለ በመሆኑ የተሻለ የማጓጓዝ ሥራ በቀጣይ ሊሠራ እንደሚችል አቶ ሲራጅ አመላክተዋል።



አቶ ሲራጅ አብዱላሂ

የወደብ ኪራይን ለመቀነስ በማሰብ ድርጅቱ በራሱ ወጪ ሀገር ውስጥ ለደረቅ ወደቦች ቅድሚያ ሰጥቶ ዕቃዎችን እያስገባ ነው፣ ነገር ግን በባለሀብቶች ዘንድ ቶሎ አለማንሳት ይስተዋላል ያሉት አቶ ሲራጅ፣ ከገቡ በኋላ ንብረታቸውን በቶሎ በማንሳት ለዘርፉ አገልገሎት መሳለጥ የበኩላቸውን ድረሻ ሊያበረክቱ ይገባል ሲሉም መክረዋል፡

# የክልሉ አርቲስቶች በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ርዳታ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን ገለጹ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች ርዳታ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ መጀመራቸውን የኦሮሞ አርቲስቶች ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴ አስታወቀ። ኮሚቴው "ዜጋ ለዜጋው ጋሻ ነው" በሚል መሪ ቃል ድጋፍ የማሰባሰብ ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገልጿል ።

በድርቅ ለተጎዱ ዜጎችን ለመርዳት በአርቲስቶች የተቋቋመው ኮሚቴ ሰብሳቢ አርቲስት ቀመር የሱፍ ሰሞኑን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤የክልሉ አርቲስቶች አንድ ላይ በመሆን በድርቅ ለተጎዱ የቦረና ፣ ጉጂ እና ባሌ ቆላማ አካባቢዎች ለሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እርዳታ የማሰባሰብ ሥራ ጀምሯል። ኮሚቴው በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች ድጋፍ እንዲደረግ የማነሳሳት ሥራ ይሠራል፣ ርዳታ በመሰብሰብ ኅብረተሰቡ ከችግሩ እስከሚላቀቅ የድረስ ድጋፍ ሥራውን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አርቲስት ቀመር ገልጿል።

ኮሚቴው የተጀመረውን ሥራ ከግቡ ለማድረስ የአጭር እና ረጅም ጊዜ እቅድ ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ያሉት ሰብሳቢው ፣ ከኅብረተሰቡ የተገኘውን ድጋፍ በማሰባሰብ በፍጥነት በድርቅ ለተጎዳው ኅብረተሰብ ማድረስ ቀዳሚ ሥራ ይሆናል። በተመሳሳይ በ15 ቀናት ውስጥ ኮንሰርት የማዘጋጀት እቅድ አለ፣ በሰፊው ኅብረተሰቡ እጁን እንዲዘረጋ ለማድረግ በክልሉ የሚገኙ አርቲስቶች ከሌሎች ክልሎች እንዲሁም በሀገር ውስጥና በውጪ ከሚኖሩ አካላት ጋር ለመሥራት ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል።

ሥራውን የበለጠ ተደራሽና ስኬታማ ለማድረግ ኮሚቴው ከኦሮሚያ ክልል ቡሳ ጎኖፋ ጋር እንደሚሠራ ገልጸው እስከ አሁን በተሠራው ሥራ ለምግብነት የሚውሉ እህሎች በቆሎ ፣ ዱቄት፣ ዘይትና በገንዘብ ለመርዳት ኅብረተሰቡ ቃል እየገባ ሲሆን የተሰበሰበው ርዳታ መጠን ሙሉ በሙሉ ኮሚቴው እጅ ሲገባ ይፋ ይደረጋል። በአርቲስቶች የተጀመረው ዜጎችን የመርዳት ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አርቲስት ቀመር ጥሪ አቅርበዋል።

የኦሮሚያ ፋይን አርት ፕሬዚዳንት አርቲስት ዑመር ጎቤ በበኩላቸው ፤ በአሁኑ ሰዓት በድርቅ የተጎዳውን የቦረና ማኅበረሰብ በመጎብኘት ላይ እንደሚገኙ ገልጸው በጉብኝታቸው ወቅት በድርቁ ምክንያት ሕዝቡ ላይ



አርቲስት ቀመር የሱፍ

እየደረሰ ያለው ችግር አስከፊ መሆኑን መረዳታቸውን ገልጸዋል። አያይዘውም በድርቁ ምክንያት እስከ አሁን ድረስ ሦስት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን እንስሳት መሞታቸውንና ከስምንት መቶ ሺህ በላይ ሰዎች ለተረጅነት መጋለጣቸውን ለተረጅነት ከተጋለጡ ውስጥም 200 ሺህ በላይ አስቸኳይ ርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው መረዳታቸውን ተናግረዋል። በተመሳሳይ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ሕጻናት እና እድሜያቸው ከ65 ዓመት በላይ የሆኑ አዛውንቶች ጉዳት እንደደረሰባቸው አይቻለሁ ብለዋል።

አርቲስት አቡሽ ዘለቀ በተመሳሳይ በድርቅ የተጎዱ ወገኖችን ለመርዳት ከአርቲስቶች ጋር በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ገልጿል። ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ጋር በመሆን ኅብረተሰቡን ከችግሩ ለመታደግ ጥረት እየተደረገ ነው። እስከ አሁን ድረስ በተደረገው እንቅስቃሴ ለምግብነት የሚውሉ እህሎች መሰብሰቡን ገልጾ በገንዘብ ለመርዳት ለሚፈልጉ ወገኖች የባንክ አካውንት እየተዘጋጀ ነው ብሏል። አርቲስቶች ባሉበት ቦታ ሆነው በድርቅ የተጎዱ ወገኖችን የመታደግ ሥራ እንዲያፋጥኑ አርቲስት አቡሽ ጥሪ አቅርቧል ።

# የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ለመሆን የሚያስችል ዝግጅት እያደረገ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ራስ ገዝ ለመሆን የሚያስችል ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ። የዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን እንደሚያሳድገው ተገልጿል።

የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጀማል ዩሱፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሟት ራስ ገዝ እንዲሆኑ የተጀመረውን ጥረት ታሳቢ በማድረግ ዩኒቨርሲቲው የራሱን ዝግጅት እያከናወነ ይገኛል።

የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ይረዳል። ያሉት ዶክተር ጀማል፤ እንደ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ የመጀመሪያው ሥራ ያደረግነው ራስ ገዝ የመሆን ሀሳቡን ሁሉም እንዲቀበለው ሃሳቡን ማስረጽ ነው። በዚህ ረገድ የተለያዩ የውይይት መድረኮችና ዝግጅቶች ተካሂደዋል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ዶክተር ጀማል ገለጻ፤ በራስ ገዝነት አስተዳደር ዙሪያ የአዕምሮ ዝግጁነት እንዲመጣ በተለያዩ መድረኮች ላይ የግንዛቤ ፈጠራ ሲሠራ ቆይቷል። በተለይም ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ ከምሥረታው ጀምሮ ከውጪ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ግንኙነት የነበረው በመሆኑ የውጪ አገር ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሲሆኑ እንዴት ሀብት ማሰባሰብ እንደቻሉና በምን መልኩ ሥርዓቱን ማስኬድ እንደቻሉ ለማወቅ የሚረዳ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።

ዩኒቨርሲቲው ያለውን የሰው አቅም በመገንባት፣ አስፈላጊ ግብዓቶችንም በማሟላትና በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችል ሥራ በመሥራት ላይ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ጀማል፤ ከዚህ ባለፈ በተጓዳኝ አገልግሎቶች የዩኒቨርሲቲውን የፋይናንስ አቅም የማጠናከር ሀብት የማመንጨት ሥራ ላይ ትኩረት መደረጉን ጠቁመዋል።

የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው አግባብ የራስ ገዝ ሆኖ መሥራት እንዲችል የሚረዳ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ዩኒቨርሲቲው በእራሱ የንግድ ድርጅት አማካኝነት ገቢ ማመንጨት የሚያስችለው ግብረ ኃይል እና መመሪያን መዘጋጀቱን ገልጸው፤ የተዘጋጀው መመሪያ በዩኒቨርሲቲው



ዶክተር ጀማል ዩሱፍ

ቦርዱ ከጸደቀው በኋላ እንደ ማንኛውም የንግድ ድርጅት ራሱን ችሎ መዋዕለነዋዮችን በማንቀሳቀስ፣ ከፍ ያሉ መሠረተ ልማቶች ላይም በመሳተፍ ሀብት እንዲያመነጭ የሚያስችል ሁኔታ ይመቻቻል ብለዋል።

በተለይም በከተሞች ላይ ኢንቨስትመንት በመሳተፍ፣ በግብርና፣ በሕክምና እና በተለያዩ ሴክተሮች ላይ ሀብት ለማመንጨት ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

የገቢ ምንጭን ከማስፋት አንጻር ዩኒቨርሲቲው ያለውን የእርሻ ሀብቶችን በመጠቀም ምርቶችን በማሰባሰብ፣ምርጥ ዘርን በማዘጋጀትና ተደራሽ በማድረግ፣ የዩኒቨርሲቲውን የጤና ማዕከል የሕክምና ቱሪዝም ማዕከል በማድረግ ረገድ ተጨማሪ ገቢ ለመፍጠር የሚያስችል ዕድል አለው ሲሉ አስረድተዋል።

የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝነት በተለይም ጥራት ያለው ምርምር ለመሥራትና ጥራት ያለው ተማሪን ለማስመረቅ እንዲሁም በራስ የፋይናስን አቅም ውሳኔዎችን ለመስጠት አቅም የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል።

በውጪ አገር ከሚኖሩ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን የትብብር ምርምሮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ በዚህ ረገድ ዩኒቨርሲቲዎችን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚረዳ እንደሆነ አመላክተዋል።

የማኅበረሰብ አገልግሎትን ከማስፋፋት አኳያ ዩኒቨርሲቲው ፍኖተ ካርታ ነድፎ እየተሠራ ነው ያሉት ዶክተር ጀማል በዚህም ማኅበረሰቡን በማሳተፍ አቅም ኖሮት እንዲሠራ ለማስቻል የራስ አቅም ግንባታ ላይ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማ
Wereta International Business PLC

# ለከባድ ተሽከርካሪ ጎማ ተጠቃሚዎች

ድርጅታችን ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ከተሰማራባቸው የሥራ ዘርፎች አንዱ የተለያየ መጠን ያላቸውን ጉማዎች ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለሽያጭ ማቅረብ ነው፡፡ በአሁኑም ወቅት ለሀገራችን መልክዓ ምድር ተስማሚ የሆነ ( TECHKING ) የተባለውን የጉማ ዓይነት በተለያየ መጠን (Size) እና ብዛት አስመጥቶ ለተጠቃሚዎች አቅርቧል፡፡

## የከባድ ጭነት ተሽከርካሪ ጎማዎች

- 12:00R20 22PR( የፊት)
- 12:00R20 22PR (የኋላ)
- 315/80R22.5 20PR (የፊትና የኋላ)

## የእርሻ ትራክተር ጎማዎች

- 14.9-24
- 12.4-24
- 14.9-30




**ይምጡና ይጐብኙን**
**በምርቶቻችን ጥራት ይረካሉ**




አድራሻ፦ ዋና መ/ቤት ቦሌ መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ኒው ብራይት ታወር ህንፃ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 301-307
☎ 0116-57 67 67 0116-63 00 20

0903-30 30 30, 0966-41 59 13, 0940-06 85 75
የሽያጭ ማዕከል፡ ቃሊቲ ሸዋ ዳቦ አካባቢ
0911 02 08 50

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትኩረት የድርቅ ተጋላጭነትን ለመቀነሱ ሥራ!

ኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ በመልካም ጉዞ ላይ ትገኛለች። እንዲያም ሆኖ ግን የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ በኩል የምርት አቅርቦትና ፍላጎት ክፍተት ሲስተዋል ቆይቷል። ይህን ክፍተት ለመሙላት እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሌሎች የምግብ ምርቶችን ጨምሮ ስንዴን ከውጭ ታስገባ ነበር።

መንግስት ይህን የአቅርቦትና ፍላጎት ክፍተት ለመሙላት፣ አገሪቱ ከውጭ የምታስገባዋን ስንዴ ለማስቀረት፣ ከዚህም አለፍ ብላ ስንዴ ለጎረቤት አገሮች ለማቅረብ፣ ግብርናው ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው ሽግግር ያለውን ፋይዳ በመመልከት በዘርፉ መጠነ ሰፊ ስራዎችን በመስራት አሁንም ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያደርገውን ርብርብ አጠናክሮ ቀጥሏል። ይህን ተከትሎም የምርትና ምርታማነት ዕድገት እየተመዘገበ ነው።

በመኸርና በበልግ ከሚካሄደው የእርሻ ስራ በተጨማሪ በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት እየተከናወነ ያለው ተግባርና እየተመዘገበ ያለው ውጤት ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል። አገሪቱ ባለፈው የመኸር ወቅት ብቻ ከ110 ሚሊየን ኩንታል በላይ ስንዴ ማምረት ችላለች። በተመሳሳይ ዓመት ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 26 ሚሊየን ኩንታል አምርታለች፤ በ2015 በጀት ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ለማምረት አቅዳ መስራቱን ተያይዛዋለች።

በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት በግብርናው ዘርፍ እየታየ ያለው ለውጥ አገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ታሪክ መስራት እንደምትችል ጠቁሟል። የስንዴ ምርት መጠን እየጨመረ መምጣት፣ ዓመታዊ የስንዴ ፍጆታዋን ሸፍና ከውጭ ስንዴ ለማስገባት ታወጣ የነበረውን እስከ ሰባት መቶ ሚሊየን ዶላር ወጪ ማስቀረቷ፣ ስንዴ ለጎረቤት አገሮች መላክ ውስጥ መግባቷ ሲታሰብ በእርግጥም አገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ታላቅ እምርታ ማስመዝገብ እንደምትችል ያሳያል።

ግብርናው ከተበጣጠሰ ማሳ የአስተራረስ ዘዴ የእርሻ ስራውን በሜካናይዜሽን በማስደገፍ ማከናወን እንዲቻል አስተዋጽኦ ወደ ሚያደርገው ኩታ ገጠም እርሻ እየተሸጋገረ መሆኑ፣ የምርምር ዘርፍ ውጤቶችን መጠቀም መቻሉ፣ የውሃ አማራጮችን በሚገባ ስራ ላይ ማዋል መጀመሩና የመንግስት ቁርጠኝነት ለምርትና ምርታማነቱ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣት አስተዋጽኦ ካበረከቱት መካከል ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በአገሪቱ ምርትና ምርታማነት ቢጨምርም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ድርቅ ዜጎቿን እየጎዳባት የምትገኝ አገር ናት። እርግጥ ነው አገሪቱ የድርቅ አደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስ በተፋሰስ ልማት እና በሴፍቲኔት መርሀ ግብር ላይ ስትሰራ ቆይታለች። በዚህም የዜጎችን የድርቅ ተጋላጭነት መቀነስ የተቻለባቸው አካባቢዎች እንዳሉ ይታወቃል። ከድርቁ መመላለስ እና ብርታት ጋር በተያያዘ ግን ድርቅ የሚያስከትለው ችግር አሁንም ቀጥሏል።

ባለፉት ዓመታት በሶማሌና አሮሚያ ክልሎች በተከሰተው ድርቅ በርካታ ህዝብ ለተረጂነት መዳረጉ እንዲሁም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እንስሳት ማለቃቸው ይታወሳል። ዘንድሮም በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በተከሰተ ድርቅ ዜጎች እርዳታ ለመጠበቅ ተገደዋል፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ከብቶችም ማለቃቸውን ነው መረጃዎች ያመለከቱት።

ድርቁ በአጠቃላይ በዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የተከሰተ ቢሆንም፣ አደጋው በዜጎች ያደረሰው ችግር ሲታሰብ የድርቅ ተጋላጭነትን በመቀነስ ላይ በስፋት እንዳልተሰራም ይጠቁማል። ችግሩ እያደረሰ ያለው ጉዳት አሁንም የተጠናከረ የድርቅ ተጋላጭነትን የሚቀንስ ስራ መስራትን እንደሚፈልግ ድርቁ ቦረና ዞን ካደረሰው ጉዳት መረዳት ይቻላል።

አሁን በድርቁ ጉዳት ለደረሰባቸው አርሶ እና አርብቶ አደሮች የርዳታ አቅርቦት እየደረሳቸው ይገኛል። በቀጣይም በተጠናከረ መልኩ መድረስ ይኖርበታል። ይህ ጊዜያዊ መፍትሄ ነው፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ርብርብ ማድረግም ያስፈልጋል። እስከ አሁን ሲከናወኑ የቆዩ የድርቅ ተጋላጭነትን የመቀነስ ስራዎችን ማጠናከሩ አንድ ስራ ነው፤ አገሪቱ የድርቅ አደጋ ተጋላጭነትን የመቀነስ ስራውን በእጅጉ ማስፋት የግድ በሚላት ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች።

ለዚህ ደግሞ በበጋ ስንዴ መስኖ ልማት የተገኘውን ተሞክሮ በተለይ የውሃ ልማት ስራዎቹን ወደ ድርቅ ተጋላጭ አካባቢዎች ማስፋት ያስፈልጋል። የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ለማካሄድ ወንዞችን፣ የጥልቅ ውሃ ጉድጓዶችን፣ ሀይቆችን ለመስኖ ልማት ማዋል ውስጥ ተገብቷል። በዚህም የሚታይ ለውጥ ማምጣትም ተችሏል። በልማቱ የተገኘውን ተሞክሮ በማስፋት ድርቅን የመቋቋም አቅምን መገንባት ይገባል።

ድርቅ የሚመላለስባቸውን አካባቢዎች ማጥናት፣ ለበጋ መስኖ ስራ ላይ የዋሉ የውሃ አማራጮችን በእነዚህ አካባቢዎች ማፈላለግና ማልማት ላይ በትኩረት መሰራት ያስፈልጋል። በተለይ በክረምት ወቅት በከንቱ የሚፈሰውን ውሃ ማቆር ላይ በስፋት መስራት፣ ለእዚህም ትላልቅ ግድቦችን መገንባት፣ በዚህ የሚጠራቀመውን ውሃም ወደ ተለያዩ የአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ አካባቢዎች በማድረስ በእርሻ ስራ በስፋት ማሰማራት፣ ከብቶቻቸውን መታደግ ያስፈልጋል።

በቦረና በአንድ ወቅት ተጀምረው የነበሩ የጥልቅ ውሃ ጉድጓድ የማልማት ስራዎች ምን ደረጃ አንደደረሱ በመመርመር እና ተሞክሮ በመቅሰም፣ መስፋት ያለባቸውን በማስፋፋት፣ የድርቅ ተጋላጭነትን ለመቀነሱ ስራ ማዋል ያስፈልጋል።

አገሪቱ ያላት ሰፊ የውሃ አቅም ሀብት አውጥቶ በመጠቀም ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ስራዎች ይመሰክራሉ። ለዚህ ስራ የማንንም አገር ተሞክሮ ፍለጋና ቅመራ መሄድ አያስፈልግም። አገሪቱ የራሷ አገር በቀል ተሞክሮዎች ሞልተዋታልና። እነዚህን ተሞክሮዎች ማስፋት ብቻውን የድርቅ ተጋላጭነትን በመቀነስ የዜጎችን ህይወትና የእንስሳት ሀብትን በወሳኝ መልኩ መታደግ ይቻላል።

በግብርናው ዘርፍ ታስቦባቸው የማያውቁ እንደ በጋ ስንዴ መስኖ ልማት ባሉት ላይ በመስራት ውጤታማ መሆን ተችሏል፤ በድርቅ አደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ ላይም ተመሳሳይ ስራ በማከናወን ዘላቂ መፍትሄ ማስቀመጥ ይገባል።

በእዚህ በኩል የቆላማ አካባቢዎችና የመስኖ ልማት ሚኒስቴር ወደየትም የማይገፋው ሰፊ የቤት ስራ ከፊቱ ተቀምጦለታል። ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎችን በጥናት መለየት ይኖርበታል፤ የውሃ አማራጮችን እንዲሁ በጥናት በመለየት ማልማትና በየአርሶ እና አርብቶ አደሩ መንደር ማድረስ ላይ መስራት ይጠበቅበታል። ለእዚህም የመንግስትን፣ የለጋሾችን፣ የመላ ሕዝቡን ተሳትፎና ትብብር ማጎልበት ያስፈልጋል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዓድዋን ማባከናችን የሚቆጨን መቼ ይሆን?

አንተነህ ቸሬ

ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ወራሪ ሰራዊት ላይ ያስመዘገበችው አንጸባራቂው የዓድዋ ድል ዛሬ፣ የካቲት 23 ቀን 2015 ዓ.ም፣ 127 ዓመት ሞላው። ታላቁ የዓድዋ ድል ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረገና ኢትዮጵያና ድሏ የጭቁኖች የነፃነት ምልክትና መሰረት ሆነው እንዲታዩ ያስቻለ እንዲሁም መላውን ዓለም ያስገረመ ደማቅ ታሪክ በመሆኑ ተደጋግሞ ሊዘከርና ሊዘመርለት ይገባል።

የዓድዋ ድል ለጥቁሮች፣ በተለይም ለአፍሪካውያን፣ የነፃነት ትግል ስለነበረው ፋይዳ ተናግረው የማይጠግቡት የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚደንት ታቦ ምቤኪ ‹‹የዓድዋ ድል ለትናንት ድሎቻችን ብቻም ሳይሆን ልናሳካቸው ላሰብናቸው አፍሪካዊ እቅዶቻችን ስኬት ታላቅ ስንቅ የሚሆነን አኩሪ ድል ነው›› በማለት በተደጋጋሚ ይናገራሉ፤ ይህን የሚናገሩት ደግሞ የድሉ መታሰቢያ መከበር ከድሉ መንፈስና ዓላማ ለመነጨት አፍሪካዊ እቅዶች ስኬት ትልቅ አበርክቶ እንደሚኖረው በማመን ነው።

የዓድዋን ድል ስናስብ ጥያቄ የሚያጭሩ ብዙ ጉዳዮች አሉ። የዓድዋ ድል ትርጉሙና በረከቶቹ ብዙ ናቸው፤ ከእነዚህም መካከል ዓድዋና ያለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ጉዞ፣ የዓድዋ ድል አከባበር እና ተያያዥ ጉዳዮች የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

የዓድዋ ድል ያስገኛቸውን በረከቶች በሚገባ እንዳላወቅናቸውና እንዳልተጠቀምንባቸው በፅኑ ከሚያምኑና ከሚሞግቱ ሰዎች መካከል አንዱ ነኝ። ሃሳቤን ለማስረዳት በቅድሚያ ድሉ ካስገኛቸው በረከቶች መካከል ጥቂቶቹን በማስረጃ አስደግፌ ላቅርብ።

በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የተመራው የኢትዮጵያ ጦር በወራሪው የኢጣሊያ መንግሥት ጦር ላይ ያስመዘገበው ድል በዓይነቱ የተለየ ስለነበር መላውን ዓለም ያስገረመ፣ ያስደነቀና ያስደነገጠ ክስተት ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል። ይህ ድል ከኢትዮጵያ አልፎ ለመላው ዓለም ጭቁኖች የነፃነት ተስፋን የፈነጠቀና ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረገ፤ በአንፃሩ ለወራሪው ጦር ደግሞ ሁለገብ ውድመትንና ውርደትን ያስከተለ ድል ነው።

የዓድዋ ድል የአፍሪካ የፀረ-ቅኝ ግዛት ንቅናቄዎች ምልክት መሆን የቻለ ወሳኝ ታሪካዊ ክዋኔ ነው። ጦርነቱና ድሉ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ በጋራ ተሰልፈው ዓለምን ያስደነቀ ገድል መፈፀማቸውን ለመላው ዓለም ያሳዩበት በመሆኑ ጭቁን ሕዝቦች ለነፃነታቸው በጋራ ሆነው መታገል እንደሚገባቸው ትምህርት የሰጠ ታላቅ ክስተት ነው። የድሉ ትሩፋቶች ለጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ትግል ትልቅ የሞራል ስንቅ ሆነዋል፤ የነፃነት ትግሎቹም ፍሬያማ ይሆኑ ዘንድ የስኬት መንገድን ጠርገዋል።

የዓድዋ ድል በአፍሪካ፣ በካሪቢያንና በእስያ የተካሄዱ የነፃነት ትግሎች እንዲጀመሩና ስኬታማ እንዲሆኑ የጎላ ሚና ነበረው። ይህ ሚናውም በበርካታ የአገራት መሪዎች፣ ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች ተመስክሮለታል። ከአህመድ ሴኮ ቱሬ እስከ ኔልሰን ማንዴላ፣ ከክዋሜ ንክሩሁማ እስከ ታቦ ምቤኪ፣ ከዊልያም ኤድዋርድ ዱ ቦይስ እስከ ማርክስ ጋርቬይ፣ ከስቬን ሩቤንሰን እስከ ማሞ ሙጬ፣ ከዶናልድ ናታን ሌቪን እስከ አየለ በከሪ፣ ከቨርጂኒያ ሊ ጃኮብስ እስከ ሮበርት ኔስታ ማርሌይ (ቦብ) ... በርካታ የአገራት መሪዎች፣ ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች ስለዓድዋ ድል አንፀባራቂነትና በዓድዋ ስለደመቁት ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ተናግረዋል፤ ጽፈዋል፤ አዚመዋል፤ ዘፍነዋል!

ኢትዮጵያን እንደ ሁለተኛ አገራቸውና ቤታቸው የሚቆጥሯት የአፍሪካ የነፃነት መሪዎች (ኔልሰን ማንዴላ፣ ሮበርት ሙጋቤ እና ሌሎችም) የነፃነት ትግላቸውን ባደረጉባቸው ጊዜያትም ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው የተለያዩ ድጋፎችን አግኝተዋል። እንግዲህ ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ እንደነፃነት ምልክት መቆጠሯ በወሬና በንድፈ ሃሳብ የተገለፀ ብቻ ሳይሆን በተግባር የታዬና የተረጋገጠ መሆኑን ነው። የዚህ ሁሉ ምንጭ ደግሞ የዓድዋ ድል ነው። የአብዛኞቹ የዓለም የጭቁኖች የነፃነት ትግሎች መነሻና የስኬት ምንጭ የዓድዋ ድል እንደሆነ አይካድም።

የዓድዋ ድል በተለያዩ የዓለም አገሮች ለተደረጉ የነፃነት ትግሎች መነቃቂያ ከመሆን ባሻገር አገራት ነፃነታቸውን ካገኙ በኋላ በጭቁኖች ለተቋቋሙ ተቋማት መመስረትም ሚናው የጎላ ነው። ከእነዚህ ተቋማት መካከል አንዱ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (Organization of African Unity - OAU) የአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት (African Union - AU) ነው። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (Organization of African Unity) መመስረት የዓድዋ ድል ውጤት ነው። የድርጅቱን ምስረታ፣ ዋና መስሪያ ቤቱ አዲስ አበባ ላይ የመሆኑንና የአፍሪካ አገራትም በዚህ የመስማማታቸውን ነገር ከዓድዋ ድል ውጭ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፤ አይቻልምም።

ለድርጅቱ መመስረት ምክንያት የሆነው የፓን አፍሪካ ንቅናቄ (Pan-Africanism) የተጠናከረውም በዓድዋ ድል ነው። ምንም እንኳ የፓን-አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ከዓድዋ ጦርነት ቀድሞ የተጀመረ ቢሆንም፣ በዓድዋ የተገኘው ድል ግን የፓን-አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴን ይበልጥ እንዲጠናከር አድርጎታል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዓድዋ ድል ውጤት መሆኑ የዓድዋ ድል የአፍሪካውያን የነፃነት ትግሎችና ከትግሎቹ መጠናቀቅ በኋላ የተመሰረቱ ተቋማት የዓድዋ ድል ደማቅ አሻራ እንዳረፈባቸው ጠቋሚ ምስክር ነው።

የዓድዋ ድል የትብብርንና የአንድነትን ውጤታማነት እንዲሁም ለነፃነት መስዋዕትነት መክፈል ታላቅ ክብር እንደሆነ ያሳየ፣ የነጮች የበላይነት ማክተም እንደሚችልም የጠቆመና መንገድ የከፈተ አንፀባራቂ ክስተትም ነው። ይህን ክብርና መንገድ በጀግንነትና በመስዋዕትነት በታጀበ ተግባር ያሳዩትና የመሩት ኢትዮጵያውያን ደግሞ የጭቁኖች መመኪያ መሆናቸውን አስመስክረዋል።

ጥቁሮች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ሁሉ የዓድዋ ድል ትዝታና ስሜት ነበር። ጭቁኖች ኢትዮጵያን የነፃነት ምልክትና የጥቁሮች ሁለተኛ ቤት አድርገው ነው የሚመለከቷት። ‹‹ኢትዮጵያ አገራችን ናት›› ብለው ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት እንቅስቃሴ ሲያደርጉም ነበር። በተለይ ጃማይካዊው የፖለቲካ አክቲቪስትና የመብት ተሟጋች ማርክስ ጋርቬይ በንግግሩም ሆነ በጽሑፉ ላይ ሁሉ ‹‹በባርነት ተይዛችሁ በዘር አድልኦ በሽታ በተጠናወተው ኅብረተሰብ ውስጥ የምትኖሩ ጥቁር አፍሪካውያን በሙሉ ወደ አገራችሁ ወደ አፍሪካ፣ የነፃነት አገር ወደ ሆነችው አገራችሁ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ፊታችሁን ወደ ኢትዮጵያ መልሱ፤ ወደ ጥንት ርስታችሁ አፍሪካ ተመለሱ፤ ዘውዱን የደፋውን ጥቁር ንጉሥ ተመልከቱ፤ እርሱ አዳኛችን ነው›› እያለ መጥቀሱ ኢትዮጵያ የጭቁኖች ተስፋና መመኪያ ተደርጋ መቆጠሯን ያመለክታል።

በድሉ ማግሥት ታላላቅ የአውሮፓ መንግሥታት ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት መስርተዋል። ከድሉ በፊት ‹‹ኢትዮጵያውያን ኋላ ቀሮች ናቸው›› ብለው ያስቡ የነበሩ አካላት ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት መስርተው የምጣኔ ሀብትና ወታደራዊ ግንኙነት ለመፍጠር ፍላጎት አሳይተዋል። የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ዋና ከተማ (አዲስ አበባ) የብዙ አውሮፓውያን መንግሥታት ኤምባሲዎች መቀመጫ እንድትሆን እድል ፈጥሯል።

ድሉ ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት (ለከተማ እድገት መነቃቃት፣ ለመሰረተ ልማቶች መገንባትና ለሥራ እድል መፈጠር) ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር (League of Nations)ን ጨምሮ የሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት መስራች አባል እንድትሆን ድሉ ከፍተኛ ሚና ነበረው። በአጠቃላይ የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ እውቅና እንደታገኝ አስችሏታል።

ከዓድዋ ድል 40 ዓመታት በኋላ የፋሺስት ኢጣሊያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ሲፈፅም፣ የኢትዮጵያ መወረር በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ፣ በተለይም በጥቁሮችና በጭቁኖች ዘንድ ትኩረት እንዲያገኝ ያደረገው ከወረራው 40 ዓመታት ቀደም

ዓድዋን ማባከናችን ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ሁሉን አቀፍ የሽግግር ፍትሕ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጮች ላይ የግብዓት ማሰባሰቢያ ማስጀመሪያ መድረክ ትናንትና ተካሂዷል።

በመድረኩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ባስተላለፉት መልዕክት፤ በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት አብሮነታችንን የሚፈታተኑ ግጭቶች ተፈጥረዋል። ግጭቶቹን ተከትሎ የተፈጠሩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በሕግ አግባብ ለመፍታትና እርቅ ለመፈጸም ሁሉን አሳታፊ የሽግግር ፍትሕ ሂደት አስፈላጊ ነው ብለዋል።

አቶ ደመቀ እንዳስታወቁት፤ የሽግግር ፍትሕ የፖሊሲ አማራጭ መቅረቡ በቀጣይ ግጭቶችና ተያይዘው የሚከሰቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዳይስፋፉ የሚያግዝ ሥርዓት ለመፍጠር ይረዳል።

የሽግግር ፍትሕ ሂደት ፍትሕ ከመስጠትና ጥፋተኞችን ተጠያቂ ከማድረግ ባለፈ ይቅር ባይነትን መዳረሻ ማድረግ እንዳለበት ጠቁመዋል። በቀጣይ ለታቀዱ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲዎች ዝግጅትና ትግበራ ውጤታማነት የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ አስፈላጊውን ትብብር ሊያደርጉ እንደሚገባም አቶ ደመቀ አሳስበዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ ታገሰ ጫፎ በበኩላቸው፤ የሽግግር ፍትሕ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ለሰብዓዊ መብቶች መከበርና ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው ብለዋል።

በሀገራችን ከነበሩ ልምዶች ትምህርት በመውሰድ፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችንና ምክረሃሳቦችን ባካተተ መንገድ የሽግግር ፍትሕ ሀገራዊ ዐውዱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን የሚረዳ የፖሊሲ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑም አበረታች ሂደት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በግጭት ወቅቶች የተፈጠሩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ አጥፊን ተጠያቂ ከማድረግና ለተበዳይ ተገቢውን ፍትሕ ከመስጠት ባለፈ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን መግባባትን መሠረት ያደረገ የሽግግር ፍትሕ ተግባራዊ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን አባል የሆኑት ዶክተር ማርሸት ታደሰና አቶ አዲ ደቀቦ በበኩላቸው፤ በፖሊሲው ላይ ግብዓት የማሰባሰብና እንዲዳብር የማድረግ ሥራዎች በቀጣይ እንደሚከናወኑ ገልጸዋል።

በእስካሁኑ የዝግጅት ሥራ የተለያዩ ሀገራት የሽግግር ፍትሕ ሂደትና ተሞክሮ ታይቷል። ለደቡብ አፍሪካ ወይም ለሩዋንዳና ለአሜሪካ የሠራው ሂደት ለኢትዮጵያ ይሠራል ማለት ባለመሆኑ ከሀገራችን የፖለቲካና ማኅበራዊ ዐውድ ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ ለማቅረብ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

የባለሙያዎቹ ቡድኑ ባቀረበው ጥናት መሠረት በብሔራዊ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ከየትኛው ጊዜ አንስቶ የተከሰቱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች በሕግ አግባብ መመልከት እንደሚገባ ያመላከቱ አምስት የጊዜ አማራጮችን ይፋ አድርጓል።

በዚህም ሕገመንግስቱ ከፀደቀበት 1987 ዓ.ም ጀምሮ ያሉትን የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ ከ2012 የለውጥ ኃይሉ ወደሥልጣን መምጣትን ተከትሎ ያሉት እንዲሁም የተለያዩ ወቅቶችን ያካተቱ አምስት የጊዜ አማራጮችን መቅረባቸውንና የመጨረሻው ውሳኔ ግብዓት ከተሰበሰበ በኋላ እንደሚወሰን አስረድተዋል።

በመድረኩ ላይ የሶማሌ ክልል ፕሬዚዳንት ሙስጠፌ መሐመድ ባነሱት ሃሳብ ቀደም ባሉ ዓመታት የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን መመልከት ከተጀመረ ተበዳዩ እንኳ በሕይወት የማይገኝበት ሁኔታ ስለሚኖር የጊዜ ገደቡን ከአሁኑ ዘመን ጋር የተቀራረበ መሆን ይገባዋል። በተለይም ከኢሕአዴግ መንግሥት አንስቶ ያሉትን መመልከት ቢቻል አዋጭ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ከድር ጁሃር በበኩላቸው በሽግግር ፍትሕ ስርዓቱ የቆዩ ቁርሾዎችን በማንሳት የተባባሰ ችግር እንዳይፈጥር ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ዝግጅት የባለሙያዎች ቡድን ይፋ ባደረገው መረጃ መሠረት፤ የግብዓት ማሰባሰብ ሂደቱ በተለያዩ ክልሎች የሚከናወን ሲሆን፣ በአጠቃላይ 59 መድረኮች ላይ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማወያየት ተጨማሪ ግብዓት የማሰባበሰብ ሥራ ይከናወናል።

# የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ውስጥ ወደ አክሱም ለመሄድ ተሳፍሮ ያገኘነው።

ሰላም በመፈጠሩ የሕዝብ ትራንስፖርት ዳግም ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ መመለሱ ደስ ያሰኛል። ሕዝቡም ደስተኛ ነው የሚለው አቶ ብርሃነ፤ የዛሬ ዓመት በነበረው ጦርነት ሕዝቡ ለሁለት ዓመታት ያህል በእግሩና በጋሪ ከቦታ ቦታ ሲመላለስ መቆየቱን አስታውሷል። ባለፈው ዓመት የኅዳር ማሪያምን ለማክበርና በዚያውም ዘመዶችን ለመጠየቅ ከሽሬ ወደ አክሱም በእግሩ ተጓዞ አክብሮና ጠይቆ መመለሱን ገልፆልናል።

አሁን ወደ አክሱም በሕዝብ ትራንስፖርት ልሔድ ነው፤ ስለሆነም እኔም፣ እዚህ ተሽከርካሪ ውስጥ ያለን ሁላችንም ተሳፋሪዎች በሙሉ ደስተኞች ነን። ምክንያቱም ሰላም ባይፈጠር ኖሮ ወይ በእግራችን ረጅም ርቀት እንሄዳለን። ካልሆነም እንቀራን የሚለው አቶ ብርሃነ፤ የሰላምን ጥቅም የዘመድ አዝማድን ደስታም ይሁን ኀዘን ወዲያው በትራንስፖርት ሄደን ለመካፈልና ንግድ እንቅስቃሴውን የተቀላጠፈ በማድረግ ጠቅሞናል። አሁኑ የሰላምን ጥቅም ማጣጣም ጀምረናል ብሏል።

ሆኖም የታሪፍ ዋጋው ግን ከኅብረተሰቡ አቅም በላይ መሆኑን ተናግሯል፤ከዚህ ቀደም አክሱም ለመሄድ ታሪፉ 50 ብር መሆኑን አውስተው አሁን ግን በእጥፍ ጨምሯል። እንዲያውም አሽከርካሪዎቹ ነዳጅ ከመንግሥት አግኝተናል ካሉ 100ብር አጥተናል ካሉ ድግሞ 150 ብር እየከፈልን ነው። ይህ በዘላቂነት ቢስተካከል ለሕዝቡ ጥሩ ይሆናል ብሏል።

በሽረ አውቶብስ መናኸሪያ ካገኘናቸው መካከል ሊቀካህናት ናርዶስ ገብረስላሴ ሌላኛው ናቸው። ሰላም ተፈጥሮ የትራንስፖርት መደበኛ እንቅስቃሴ መጀመሩ ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል። አሁን ሰላም በመፈጠሩ ሕዝቡ ሠርቶ መብላት ወጥቶ መግባት፤ቤተ ዘመዱን መጠየቅና እንደፈለገ መንቀሳቀስ ይችላል የሚሉት ሊቀካህናት ናርዶስ፤የሕዝብ ትራንስፖርት ዳግም መጀመሩ ሕዝቡን ደስተኛ አድርጎታል። በሰላሙም ደስተኛ ነው። አሁን ይህን መልካም ፍሬ መንከባከብና መጠበቅ ይገባል ነው ያሉት። አገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ቶሎ ቢጀምር ሲሉም ጠይቀዋል ።

ለሁለት ዓመት ያለሥራ ቁመን ነበር። በዚህ ጊዜ ብዙ ችግር አሳልፈናል፤ ሰላም ባለመኖሩ ሠርተን መኖር እየቻልን ለሁለት ዓመት ያለ ሥራ ቤት በመቀመጥ አሳልፈናል የሚለው አሽከርካሪ ማንዲ ፀጋይ፤ይህ ሁሉ አልፎ አሁን ሰላም ተፈጥሮ ዳግም ወደ ሥራችን መመለሳችን በጣም ደስተኛ ነኝ ብሏል።

አንዳንዴ የነዳጅ እጥረት ተፈጥሮ ነዳጅ በጥቁር ገበያ የምንገዛበት ሁኔታ ይከሰታል እንጂ አሁን ሁሉም ነገር ወደ መስመር እየገባ ነው ያለን አሽከርካሪው፤ይህ ቢስተካከል እኛም ያልተገባ ታሪፍ ተሳፋሪውን አናስከፍልም። እናም መንግሥት አስተማማኝ የነዳጅና የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች አቅርቦት እንዲኖር ያድርግልን ነው ያለው።

ከዞን ጊዜያዊ አስተባባሪ በተገኘ መረጃ የሕዝብ መሠረታዊ አገልግሎቶች ዳግም ወደ ሥራ ተመልሰው የኅብረተሰቡን ችግር እየፈቱ ይገኛሉ።

ዋናው የኅብረተሰቡ አንዱ ችግር የትራንስፖርት አለመኖር ነው። ይህን ችግር ለመፍታት ሽረ አቅራቢያ ያሉ ወረዳዎችና ከተሞች የትራንስፖርት አገልግሎት ተጀምሮ አሁን እየሰፋና የተሽከርካሪዎች ቁጥር ቀስ በቀስ እየጨመረ መጥቶ አሁን በአማካይ በቀን 500 እስከ 800 የሚደርሱ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ተገልጿል። በሽረ ከተማም በቀን በአማካይ ከአንድ ሺህ በላይ ባጃጆች ለኅብረተሰቡ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸው የንግድ እንቅስቃሴው እንዲያንሰራራ እያደረጉ ነው ተብሏል።



# ለዓባይ ግድብ ባለፉት 7 ወራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የጽሕፈት ቤቱ የሕዝብ ግንኙትና የሚዲያ ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሐም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሰባት ወር ውስጥ 949 ሚሊየን ብር መሰብሰቡ የዘንድሮ የህዳሴ ግድብ ገቢ አሰባሰብ ሂደቱ ከፍተኛ መነቃቃት የታየበት መሆኑን ያሳያል።

ከተሰበሰበው ብር ውስጥ ከ762 ሚሊዮን ብር በላይ የሚሆነው ከሀገር ውስጥ ቦንድ ስጦታ፤ከ12 ሚሊዮን በላይ በዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭ፤ ከ87 ሚሊዮን በላይ ደግሞ ከ8100 አጭር የሞባይል መልዕክት አማካኝነት የተገኘ መሆኑን ገልጸዋል።

በጥር ወር ብቻ 81 ሚሊዮን ብር ተሰብስቧል። ከዚህ ውስጥ በአጭር የጽሑፍ መልዕክት በ8100 "A" የተሰበሰበው ገንዘብ 75 ሚሊዮን ብር ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ኃይሉ ገለጻ፤ አጠቃላይ በ8100 የተሰበሰበው በየወሩ በአማካይ 12 ሚሊዮን ሲሆን ይህም በታላቁ የህዳሴ ግድብ ላይ የኅብረተሰቡ ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ የመቀጠሉ ማሳያ ነው ብለዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት አንደኛ ዙር የዓባይ ግድብ ጉዞ በመላው ሃገሪቱ በመካሄዱ ከፍተኛ ቅስቀሳ ተደርጓል። በተለይ 8100 እና ስለቦንድ ግዢ ከፍተኛ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተደርጎ ከፍተኛ ገቢ መሰብሰብ ተችሎ እንደነበር አስታውሰዋል።

ሁለተኛው የዓባይ ግድብ የገቢ ማሰባሰቢያ ጉዞ ከሦስት ሳምንታት በፊት የተጀመረ ቢሆንም ከፍተኛ መነቃቃት ይታይበታል ሲሉ ተናግረዋል።

በአዲስ አበባ በሁለተኛው ዙር በተደረገው የዓባይ ግድብ ጉዞ መርሐግብር ሙሉ በሙሉ ማዳረስ ባይቻልም ሽፋን በተሰጣቸው ክፍለ ከተሞች ከሁለት እስከ አምስት ሚሊዮን ብር መሰብሰብ ተችሏል ሲሉ አስታውቀዋል።

የጉዞ መርሐ-ግብሩ በሦስት አቅጣጫ የሚደረግ ይሆናል ፤አሁን ላይ የዓባይ ግድብ ገቢ ማሰባሰቢያ ጉዞ አዲስ አበባ ላይ ተጠናቆ ወደ አማራ ክልል ከተሞች ተሸጋግሯል። በቀጣይም ወደ አፋር ክልል እንዲሁም ወደ ኦሮሚያ በመጓዝ በመላ ሀገሪቱ ያሉ ከ200 በላይ ወረዳዎች እንደሚያዳርስ ተናግረዋል።

የጉዞ መርሐ-ግብሩ ዋና ትኩረት በሄደባቸው መንገዶች መልዕክት የማስተላለፍና የኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዲጨምር ለማድረግ ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ በተጨማሪም ከገቢ ማሰባሰብ ጎን ለጎን ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በሀገራዊ ስሜት ወደ ሀገራዊ አጀንዳ እንዲመለስና የዜግነት አሻራውን እንዲያሳርፍ ከፍተኛ መነቃቃትን ይፈጥራል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ አክለውም፤ የዓባይ ግድብ ሰላምን የሚያሰፍንና አንድነትን የሚያጠናክር ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ በመሆኑ የሚያነጣጥሉን እኩይ አጀንዳዎች ወደ ጎን በመተው ለግድብ ግንባታ መጠናቀቅ የበኩላቸው ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የኅብረተሰብ ተሳትፎ እንዲጨምር የአመራሩም ትኩረት ወደ ዓባይ ግድብ እንዲያደርግ እንዲሁም የገቢ ማሰባሰቡ እንደ አዲስ እንዲነቃቃ የውይይት መድረኮች ለማዘጋጀት በዕቅድ ደረጃ ተይዞ እየሠራን ይገኛል ብለዋል።

የመገናኛ ብዙኃን የገቢ ማሰባሰቢያ ሥራዎች እንዲጠናከሩ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡም ዳይሬክተሩ ጥሪ አድርገዋል።

# የኢትዮጵያንና የፓኪስታንን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሞተር የሆነው ግብርናን ለማዘመን በቅድሚያ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በማኑፋክቸሪንግ፣ በማዕድንና በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ኢትዮጵያ ያልተነካ ሀብት አላት ያሉት አቶ ደመቀ፤ የዲጂታል ኢኮኖሚውን ለማዘመን እንሠራለን ሲሉ ገልጸዋል። መንግሥት ድህነትን ለማጥፋት በትኩረት እየሠራ ሲሆን የጤና፣ የንጹሕ ውሃ መጠጥ አቅርቦትና ሌሎች ተጓዳኝ ሥራዎችን በፍጥነትና በስፋት እያከናወነ እንደሚገኝ ገለጻ አድርገውላቸዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ ከግብርና እስከ ቱሪዝም ከፍተኛ ሀብት ስላላት የፓኪስታን ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ኢንቨስት ማድረግ ቢችሉ በእጅጉ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይሄንን ግንኙነት የበለጠ በኢኮኖሚና በተለያዩ ዘርፎች ለማጠናከር ጠንካራ ሥራ እየተሠራ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ልክ እንደ ፓኪስታን ሕዝብ እንግዳ ተቀባይ መሆኑ ለኢንቨስተሮች ጠቃሚ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥትም አስፈላጊው ሁሉ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

በኢትዮጵያ የፓኪስታን አምባሳደር ሻዛብ አባስ እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ የዓለምአቀፍ የዲፕሎማሲ መናኸሪያ ናት። ሁለቱ ሀገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ግንኙነት ተፈጥሯል።

የፓኪስታን ባለሀብቶች በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ዘርፍ መሠማራት ይፈልጋሉ ያሉት አምባሳደር ሻዛብ፤ ኢትዮጵያ የሥልጣኔ ምልክት መሆኗን ገልጸው የሕዝቧ እንግዳ ተቀባይነት፣ ምቹ የአየር ንብረት መኖሩና የዲፕሎማቲክ ማዕከል መሆኗ ኢንቨስተሮች ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያና በፓኪስታን መካከል ያለውን የቆየ ግንኙነት ለማጠናከር በሁለቱ መንግሥታት መካከል ብዙ ሥራዎች መኖራቸውን ያነሱት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማንነት ያላቸው ሰዎች በሰላምና በወንድማማችነት የሚኖሩባት ሀገር መሆኗን ገልጸዋል። እንዲሁም የሰው ልጅ የሚከበርባትና ለሁሉም አይነት ሥራ ምቹ መሆኗን አስረድተው ግንኙነቱን ይበልጥ ለማጠናከር እንሠራለን ብለዋል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የዲጂታል ቴክኖሎጂ ግብይት - የአዳዲስ ፈጠራ ሀሳቦች ውጤት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በአገሪቱ ሀሳቦች ሀሳብ ከመሆን አልፈው ተገቢውን ድጋፍ አግኝተው እንዲያድጉና እንዲበለጽጉ በማድረግ ረገድ በርካታ ተግባሮች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ይህን ተከትሎም ዲጅታል ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ በማዋል የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት ኑሮ ቀላል የሚያደርጉ አገር በቀል የፈጠራ ውጤቶች ብቅ ብቅ እያሉ ይገኛሉ።

ሀሳብ ያላቸው ዜጎች ሀሳብ እንዲያድግ በመደገፍ ሀሳባቸውን ወደ ቢዝነስ የሚለውጡባቸው ሁኔታዎች እየተመቻቹ መሆናቸውን ተከትሎ ያላቸውን እውቀት ተጠቅመው ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት የሚደረገውን ሂደት ለመደገፍ ጥረት እያደረጉ ያሉ ስታርታፖች በየቢዝነስ ዘርፎቹ ተሰማርተው ይታያሉ።

በመንግሥት በኩል የስታርታፕ ምህዳር እንዲሰፋ በማድረግ ረገድ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። በዚህም የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ድርጅት ጋር በመተባበር የስታርታፕ ኢኮሲስተም ተዋንያን የምክክር መድረክና የዲጅታል ስታርታፕ ኢግዚቢሽን የካቲት 13 እና 14 በሳይንስና አርት ሙዚየም አዘጋጅተው ነበር። በኢግዚ,ቢሽኑ የተሳተፉ ስታርታፖች እንዳሉት፤ በስታርታፖች እየተፈጠሩ ያሉ ስራዎች ለማህበረሰቡ መረጃ በማድረስ፣ ሊደርስበት የሚችለውን እንግልት በመቀነስ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ናቸው። ስራ ከመፍጠራቸው በተጨማሪ ለሌሎች ዜጎችም የስራ እድል እየፈጠሩ ይገኛሉ።

ዩቶጵያ ኢ-ፋርማሲ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኢግዚቢሽኑ ተሳትፏል፤ የድርጅቱ የጥሪ ማዕከል ሠራተኛ ወጣት ቢቂላ ወንድሙ እንደገለጸው፤ አግዚቢሽኑ በአይነቱ ልዩ የሆነ የመድኃኒት ግብይትን ቀላል የሚያደርግ በኢትዮጵያውያንና በአሜሪካውያን የበለጸገ መተግበሪያና ጽረገጽ ይዘው ቀርበዋል። ይህ ዲጅታል ፕላትፎርም አርቲፊሻል ኢንተለጀስን ጨምሮ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዲጅታል መድኃኒት መፈለጊያ፣ ማዘዣ እና የፋርማሲ መረጃ አገልግሎት የሚሰጥ ሞባይል መተግበሪያም አለው።

በዚህ «ሃሎ መድኃኒት» የተሰኘ መተግበሪያ አንድ ሰው መድኃኒት ሲፈልግ በስልክ ቁጥር 9640 በመደወል ወይም መተግበሪያውን ከጉግል ወይም ከአፕስቶር በማውረድ የሐኪም ማዘዣውን እስካን አድርጎ ወደኛ ሲልክ እኛ በአቅራቢያው መድኃኒቱ የሚገኝበትን ፋርማሲ አፈላልገን በደቂቃ ውስጥ እንዲያገኝ እናደርጋለን ሲል ወጣት ቢቂላ ይናገራል። ስለመድኃኒቶቹ የጎንዮሽ ጉዳትና ተያያዥ ጥያቄዎች የሚያነሳም ከሆነ አስተማማኝ መረጃ ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ መፈጠሩን ይገልጻል። ቤቱ ሆኖ የመድኃኒት አቅርቦት የሚፈልግ ሰው ካለ ደግሞ ያለበት ድረስ የሚፈልገውን መጽኃኒት እናቀርባለን ይላል።

ከዚህ በተጨማሪ ከፋርማሲ ፋርማሲ የመድኃኒት የዋጋ ልዩነት ስላለ መድኃኒቱ ያለባቸውን ፋርማሲዎች የመድኃኒት ዋጋ በመጥቀስ ሰዎች በተሻለው ዋጋ መድኃኒት እንዲያገኙ የሚያደርግ መተግበሪያ መሆኑንም ያብራራል።

ወጣት ቢቂላ እንደሚለው፤ ዲጅታል መተግበሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ ፋርማሲዎችን ወደዚህ ሲስተም ለማስገባት ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል። አሁን በአዲስ አበባ በየክፍለ ከተማው አሥር የሚጠጉ አባል ፋርማሲዎች አሉ። ቁጥራቸው እየጨመረ ይሄዳል። ህብረተሰቡ ግንዛቤ ስለሌለው እንጂ አገልግሎቱን ይፈልገዋል።

ለዚህም ማሳያው በተለይ መድኃኒት ፍለጋ ደክመው ያጡ ሰዎች እኛ ዘንድ ደውለው ይህንን አይነት መድኃኒት ብዙ ቀን ፈልገን አጣን፤ እናንተ ታገኙት ከሆነ እባካችሁን አፋልጉን ሲሉ ይጠይቃሉ ያለው ወጣት ቢቂላ፣ ‹‹እኛ በ10 እና በ15 ደቂቃ ፈልገን ስናገኝላቸው እንዲህም አለ እንዴ! በማለት በመገረም ጭምር እንደሚናገሩ ጠቅሶ፣ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እየጠየቁ መሆናቸውን እንደሚገልጹም ይናገራል። ህብረተሰቡ የመተግበሪያውን ጥቅም ባወቀ መጠን የአገልግሎቱ ፈላጊ እንደሚሆን ይገልጻል።

**አዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎችን ከማበረታታትና የገበያ ትስስር ከማስፋት አንጻር የዲጂታል ግብይት ወሳኝ ሚና ይጫወታል። እንደ አገር የህብረተሰቡን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚያግዙ የፈጠራ ሥራዎች እያደጉ መጥተዋል። እነዚህ የፈጠራ ሥራዎች ወደ ተግባር ተለውጠው ውጤት እንዲያመጡ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን መወጣት አለባቸው**

ድርጅቱ ለስድስት ሠራተኞች የሥራ እድል የፈጠረ ሲሆን፤ ዲጅታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአገራችንን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽነትና ጥራት ለማዘመን ይሰራል። ወደፊት ተለምዷዊ አካሄዶችን ወደ ዲጅታል በመቀየር ቀላል በሆነ መልኩ ሕይወት መምራት እንዲቻል እንሰራለን የሚለው ወጣት በቂላ፤ ይህንንም ወደ ክልሎች ድረስ በማስፋት ሰዎች መድኃኒት እያለ በመድኃኒት እጦት የሚደርስባቸው እንግልት መቀነስ እንደሚያስፈልግ ያመለክታል።

ሰዎች ስለመድኃኒት ማንኛውንም የተሟላ መረጃ ማወቅ ከፈለጉ ሃሎ መድኃኒት ማለት ይችላሉ የሚለው ወጣት ቢቂላ፤ ሁልጊዜም ከጠዋቱ ሁለት ተኩል ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ተኩል በቀጥታ /ኦንላይን/ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ ብሏል።

ሌላኛዋ የፍሪላንስ ሥራ ድርጅት መስራችና ጀነራል ማናጀር ቤዛዊት አድማሱ በበኩሏ በትርፍ ጊዜ የሚሰሩ ሥራዎችን የሚያመቻች አንላይን ፕላትፎርም ያለው ‹‹ፍሪላንስ ሥራ ዶት ኮም›› የተሰኘ ጽረገጽ ይዛ በኤግዚቢሽኑ ቀርባለች። ‹‹ፍሪላንስ ሥራ›› የተሰኘው ዲጅታል መተግበሪያ ባለሙያዎች (ፕሮፌሽናሎች) እና የፍሪላንስ ሥራን ያገናኛል። ይህን ሥራ የጀመርነው ያቀረብነው ሀሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ድጋፍ ከተደረገልን በኋላ ወደ ቢዝነስ እንዲዳብር ተደርጎ ነው የምትለው ቤዛዊት፤ እንደ ስታርታፕ የጀመሩት መሆኑንና ዓመት እንዳልሞላውም ትናገራለች። ዛሬም በዚህ ኤግዚቪሽን የተሳተፉት የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት (UNDP) የገንዘብ ድጋፍና በሥራ ፈጠራና ክህሎት ሚኒስቴር በተደረገላቸው ድጋፍ መሆኑን ትገልጻለች።

ቤዛዊት እንደምትለው፤ ጽረገጹ ተሰርቶ ሥራ ከጀመረ አንስቶ ወደ አንድ ሺ የትርፍ ጊዜ ሥራ ፈላጊዎችን (ፊሪላንሰሮች) አሉት። ድርጅቱ በጽረገጹ በተለያየ የትምህርት መስክ ተምረው ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን ግለታሪክ አደራጅቶ አስቀምጧል።

አሳሪዎች የአጭር ጊዜ ሥራ ማሰራት ሲፈልጉ ጽረ ገጽ ላይ ይገቡና የሚፈልጉትን ሲመርጡ እኛ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን። በሁለቱ መካከል ያለውን ስምምነትም እንከታተላለን የምትለው ቤዛዊት፣ ሥራው ተሰርቶ እስከሚያልቅ ድረስ የድጋፍና የክትትል ስራ እንደሚሰሩ ታብረራራለች። የትርፍ ሰዓት ሥራ ተጠቃሚውም ሆነ አሰሪው ደስተኛ ሆነው ክፍያቸውን ፈፅመው እንዲሄዱ እንደሚያደርግ ጠቅሳ፣ ሥራዎች ቀላል እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል መተግበሪያ መሆኑን ትጠቁማለች።

እንደ እሷ ገለጻ፤ መተግበሪያው ለባለሙያዎች እዚያ ቦታ የግድ ተቀጥረው መሥራት ሳይጠበቅባቸው በትርፍ ጊዜያቸው፣ በእረፍት እና በበዓል ቀናት በአንድ ከተማም ባይሆኑ በርቀት በክልሎች ሆነ ከአገር ውጪ በሙያቸው እየሰሩ ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች ነው።

እስካሁን ጀማሪ እንደመሆናችን መጠን ያሰራናቸው ጥቂት ሰዎችን ቢሆንም፣ ሁሉም ግን ደስተኞች ናቸው የምትለው ቤዛዊት፤ ለአብነት አንድ እናት ቤቷ ቁጭ ብላ ልጇን እያሳደገች እውቀቷ በጣም የሚፈለግ ድርጅት ደግሞ እኛ ጋ መጣና ሥራ ተሰጣት እሷም ቤቷ ልጇ አጠገብ ሆና በሚመቻት ሰዓት ሥራውን ሠርታ አስረከበች፤ ተከፈላት። ያቺ እናት በጣም ደስተኛ ነበረች ስትል አብራርታ፣ ፍሪላንስ ስራ እንደዚህ አይነት እርካታ የሚፈጥር ሥራ መሆኑን አስታውቃለች። አሰሪውም የሚፈልገውን እውቀት በፈለገበት ጊዜ ማግኘቱ ሌላ እርካታ እንደሚፈጥር ትናገራለች።

በዚህ ሥራ ላይ ብዙ ተግዳሮቶች እንዳሉም ጠቁማለች። በኛ አገር እንደዚህ አይነት ሥራ መሥራት አልተለመደም፤ ሥራዎችን ኮንትራት እንኳን ወስዶ በሰዓቱ ያለማስረከብ ችግሮች መኖራቸውን ትናገራለች። በኮቪድ ወቅት በርቀት መሥራት እንደሚቻል ተለማምደናል የምትለው ቤዛዊት፤ ያ ወቅት ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ሥራዎችን ሠርቶ ማስረከብ እንደሚቻል አሳይቶናል ትላለች።

ቤዛዊት ‹‹ በቴክኖሎጂ ረገድ ብዙ የሚቀሩ ነገሮች ቢኖሩም፣ በተቻለ መጠን ደንበኞች ላለማስከፈት ማድረግ የምንችለውን እናደርጋለን›› ስትል ገልጻለች። ሠርተው ስኬታማ የሆኑትን እንደ ማሳያ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ እንደሚያደርጉም ነው የተናገረችው።

አሁን ላይ በኦንላይን የሚሰሩ ሥራዎች በጣም እየተለመዱ ናቸው። በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። ቴክኖሎጂውን አንዱ እየተጠቀመ አንዱ ደግሞ በጊዜ ባለማስከረብ እየተጎዳ መሆኑን ሲያየው ሰው ራሱ ወደ መስመር እየገባ ይመጣል።

በአገሪቱ አሁን የኢንተርኔት ተደራሽነትም በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ሳፋሪኮም መምጣቱም ትልቅ እድል ይፈጥራል። እንደ ድሮ ወደ ውጪ መውጣት ሳያስፈልግ በቤቱ በሞባይል ስልኩ ላይ ኢንተርኔት በመጠቀም ብዙ ነገሮችን በቀላሉ ማግኘት ይቻላል። በዚህ ረገድ ወደፊት በመጓዝ የስኬታችንን ልምድ እያካፈልን ከተጓዝን ለውጥ ይመጣል ስትል ታብራራለች።

እስካሁን ከመቶ በላይ ሥራዎችን መፍጠር ችለናል የምትለው ቤዛዊት፤ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ሥራዎች የሰራበት ሁኔታ መኖሩን ትናገራለች። አሁን ከፕላትፎርማችን ላይ ሥራ ለመውሰድ ዝግጁ የሆኑ አንድ ሺ የሚጠጉ ሥራ ፈላጊዎች መኖራቸውን ጠቅሳ፤ እንደ ኩባንያ የተመዘገቡ አጋሮችና ደንበኞች ያሏቸው መሆኑን ጠቁማለች። ባለሙያዎች ደግሞ ተቀጥረው ከሚሰሩበት ውጪ ሌላ እውቀት ካላቸው መስራት የሚችሉት ሥራ በመዘርዘር ፖስት ሲያደርጉት ቀጣሪዎች ያዩታል እና ሥራ ያገኛሉ። ሰዎች www.freelansira.com የተሰኘውን ፕላት ፎርማችንን ተጠቅመው እንደቀጣሪም እንደፊሪላንሰርም ሊመዘገቡ ይችላሉ ብላለች።

ሌላኛዋ ‹‹ማረፊያ አለ›› የተሰኘ ፕላትፎርም ይዛ የቀረበችው ጽዮን ፍቃዱ ይህ ዲጅታል ቴክኖሎጂ ሰዎችን ከእንግልትና ከአላስፈላጊ ወጪ እንደሚታደግ ትናገራለች። እንደ ‹‹ማረፊያ አለ›› ለህብረተሰቡ ከፍተኛ ጠቀሜታን የሚሰጥ ሕይወትን ቀላል የሚያደርግ ነው። ጽዮን ገለጻ፤ በዚህ የቴክኖሎጂ ዘመን ማንኛውም ሰው ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ታክሲ፣ ምግብ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ አገልግሎቶች ባለበት ሆኖ ማግኘት ይችላል።

‹‹እኛ ይዘን የመጣነው አገልግሎት ደግሞ መኝታ፣ ማረፊያ ገስት ሀውሶችን፣ ትላልቅ ሆቴሎች፣ ሎጆች እና የመሳሰሉትን ሁሉንም አጠቃሎ የያዘ ስለሆነ ሰዎች የት ማረፍ እንዳለባቸው ሳይጉላሉ ወስነው ከከተማ ሲወጡም ሆነ እዚሁ ከተማ ውስጥ ሆነው ሊሆን ይችላል የት መሄድ እንዳለባቸው አስቦ ለመውጣት የሚያስችል ነው›› ስትል ታብራራለች።

እንደ እሷ ገለጻ፤ ‹‹ማረፊያ አለ›› የተሰኘው ፕላትፎርም አገልግሎት ፈላጊዎች ሆቴሎችን በተለያየ አማራጮች እንዲሁም በቦታቸውና በዋጋቸው መምረጥ የሚችሉበት ነው። ይህ ፕላትፎርም በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ ወደ 65 ከተሞች የሚገኙ የሆቴሎችን ዳታ የያዘ መተግበሪና ድረገጽ አለው። በተጨማሪም 9717 የስልክ አገልግሎትም የሚሰጥ ሲሆን፤ ሰዎች የማረፊያ አገልግሎቶችን በመፈለግ የሚደርስባቸውን መጉላላት ይቀንሳል።

እነ ጽዮን ሥራውን ከጀመሩ አንድ ዓመት ሞልቷቸዋል፤ አሁን ተደራሽነታቸውም በከፍተኛ ሁኔታ ሰፍቷል። ሁለት ሺ አምስት መቶ የሚጠጉ ሆቴሎችን መረጃም ይዘዋል። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ 50ሺ የሚጠጉ ሰዎች መተግበሪያውን አውርደው እየተጠቀሙት ነው። የድረ ገጽ እና የስልክ መስመሩን የሚጠቀሙ ደንበኞችም አሉ።

አሁን ይህንን አገልግሎት እየተጠቀሙ ያሉት የአገር ውስጥ ደንበኞች መሆናቸው የምትናገረው ጽዮን፤ አድማሱን ለማስፋት እየተሰራ እንደሆነ ትገልጻለች። መተግበሪያው ላይ የተለያዩ ማስታወቂያ ቦታዎችን በመሸጥ እንጠቀማለን። ወደፊት የምንፈጥራቸው የክፍያ ሲስተሞች ይኖራሉ የምትለው ጽዮን፣ በዚህ ድርጅት ሥር ለ25 ሰዎች የሥራ እድል መፍጠር ተችሏል ትላለች።

በኤግዚቢሽኑ መክፈቻ ላይ የተገኙት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ባይሳ በዳዳ እንደተናገሩት፤ የአገር በቀል ቴክኖሎጂ ፈጠራ ውጤቶች ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና አላቸው። ከዚህ አኳያ የአገር በቀል የፈጠራ ሥራዎችን የሚያበረታቱ ልዩ ልዩ የህግ ማዕቀፎችን እየተዘጋጁ መሆናቸውን አመላክተዋል። ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ እንዲሁም የማህበረሰቡን አኗኗር የሚያቀሉ የፈጠራ ሥራዎች ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል።

የስራና ክህሎት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን በበኩላቸው፤ አዳዲስ ስራ ፈጣሪዎችን ከማበረታታትና የገበያ ትስስር ከማስፋት አንጻር የዲጂታል ግብይት ወሳኝ ሚና እንዳለው ተናግረዋል። እንደ አገር የህብረተሰቡን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚያግዙ የፈጠራ ሥራዎች እያደጉ መምጣታቸውንም ጠቅሰው፣ እነዚህ የፈጠራ ሥራዎች ወደ ተግባር ተለውጠው ውጤት እንዲያመጡ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን መወጣት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ከቀረጥ ነጻ የገበያ እድል በስተጀርባ

**አስቴር ኤልያስ**

ግማሽ ክፍለ ዘመን ያስቆጠረው የኢትዮጵያ እና የቻይና ግንኙነት ዘርፈ ብዙ መልክ እንዳለው ይታመናል። ስትራቴጂካዊው የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ዛሬ ላይም ተጠናክሮ በንግድ ግንኙነቱ መሰረቱን በመጣል ላይ ይገኛል። በተለይም ቻይና፣ ልክ ለሌሎቹ የአፍሪካ ሀገር እንደተሰጠው አይነት እድል ኢትዮጵያም ምርቶቿን ከቀረጥ ነጻ ወደ ቻይና እንድታስገባ መፈቀዷ የሁለቱን ሀገራት ወዳጅነት ከፍ እንደሚያደርገውም እየተነገረ ነው።

በተያዘው ወር አጋማሽ በገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴ የተመራ ልዑክ ለይፋዊ የሥራ ጉብኝት ወደ ቻይና ባቀናበት ወቅት ኢትዮጵያ እና ቻይና የኢንቨስትመንትና የኢኮኖሚ ትብብርን ለማሳደግ የሚያስችል ቡድን ለማቋቋም የስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል። ይህን ተከትሎ ቻይና የኢትዮጵያ የወጪ ምርቶች ከቀረጥ ነጻ እንዲገቡ ፍቃድ መስጠቷንና ፈቃዱም ቻይና በቅርቡ ይፋ ባደረገችው ‹‹የአፍሪካ ልዩ ቀረጥ ማሻሻያ›› ማዕቀፍ ስር እንደሚተገበር በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዣኦ ዢዩዋን በትዊተር ገጻቸው ካሰፈሩት መረጃ ማወቅ ተችሏል።

በተመሳሳይ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር ያላት ግንኙነት ስትራቴጂካዊና ወሳኝ መሆኑን ከኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስቴር የትዊተር ገጽ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ቻይና የኢትዮጵያ ወሳኝ የልማት አጋር መሆኗንም መረጃው ያመለክታል።

የኢትዮጵያ ምርት ወደ ቻይና ገበያ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ቻይና መፍቀዷ እና የሁለቱ ሀገራት የንግድ ግንኙነት በተመለከተ ያነጋገርናቸው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ ቻይና የኢትዮጵያ ምርት ወደ ሀገሯ ገበያ ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ መፍቀዷ ለሁለቱ ሀገሮች ወዳጅነትም ሆነ ለኢትዮጵያ የበለጠ ጥቅም አለው። ይሁንና በቻይና ይሁንታ የተገኘው ነጻ እድል ብቻውን ስኬታማ ስለማያደርግ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን ከተገኘው ከቀረጥ ነጻ እድል በስተጀርባ ወደ ቻይና ገበያ የሚላኩ ምርቶች ላይ በጥራትም በብዛትም ከፍተኛ ስራ ሊሰራባቸው ይገባል።

በጉዳዩ ዙሪያ ካነጋገርናቸው የምጣኔ ሀብት ባለሙያ አምባሳደር ጥሩነህ ዜና አንዱ ናቸው። እርሳቸው በቻይና ገበያ ከቀረጥ ነጻ የሆነ እድል ማግኘት በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ትርጉሙም ሆነ ጥቅሙ ብዙ ነው ይላሉ። አንደኛ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት መልካም መሆኑን የሚያመላክት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የተሰጠው እድል ትልቅ በመሆኑ የኢትዮጵያን የገበያ መዳረሻ ያሰፋል ብለዋል።

ይሁንና ይላሉ አምባሳደሩ፣ ‹‹ኢትዮጵያ ሁልጊዜም ቢሆን ገበያ የሚቸግራት አገር አይደለችም። እንዲያም ሆኖ ግን ከቀረጥ ነጻ የሆነ የገበያ እድል ማግኘት በጣም አስፈላጊም ወሳኝም ነው። ምክንያቱም በዓለም ላይ ውድድር ስላለ ዋጋው ዝቅ ማለቱ ለገበያ መሳብ አንዱ እድል ነው ይላሉ።

በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ሞገስ ቱፋ በበኩላቸው፣ ነጻ እድል ማግኘቱ አንድ በጎ ነገር ነው። ይሁንና የተሰጠውን እድል በአግባቡ ለመጠቀም ሁለንተናዊ ዝግጁነት ያስፈልጋል። ይኸውም በነጻ እድል የተሰጠው የምርት አይነት ወደ ቻይና ገበያ ሲላክ ጥራቱን የጠበቀ አድርጎ መስራት የግድ ይላል ሲሉ ይናገራሉ።

የመጀመሪያው ነገር የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ማለትም የእድል ሰጪ ሀገርን ፍላጎት በማሟላት የእድሉ ተጠቃሚ መሆን የግድ ነው። ስለሆነም ከጥራት ጋር ተያይዘው ያሉ ነገሮች በትኩረት ሊሰራባቸው ያስፈልጋል። ምርቱ ወደተላከበት ሀገር ደርሶ መፈተሹ ስለማይቀር ሲታይና ሲመረመር ጥራቱ የተጠበቀ ምርት እንዲሆን መስራት የግድ እንደሚል ተናግረዋል።



እርሳቸው እንደሚሉት፣ አንድ ምርት ሲመረት ማሟላት የሚገባው የጥራት ደረጃዎች አሉ። ጥራት ማለት የተጠቃሚውን ፍላጎት ማሟላት ነው። በኢትዮጵያ ለምሳሌ ወደምርት ከመግባታችን በፊት መሟላት ይገባቸዋል ተብሎ በሕግ የተቀመጡ የቴክኒክ ጉዳዮች አሉ። የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ኤጀንሲ የሚያስቀምጣቸው የጥራት ደረጃዎች አሉ። የኢትዮጵያ ደረጃዎች ቁጥጥር ባለስልጣንም የሚሰጣቸው ደረጃዎችም ይኖራሉ። እሱ ደረጃ ከዓለም አቀፉ ደረጃዎች ጋር በመሆን የተሰራ ደረጃ ነው።

ይሁንና ይህ የተባለው ደረጃ ተሟልቶ ቢገኝም ቻይና እንደገና የራሷ መስፈርት ሊኖራት ይችላል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ምርት እነዚህን ሁለቱንም ደረጃዎች በማጣመር የሚሰራ ከሆነ እሰየው ነው ሲሉ ያስረዳሉ። ነገር ግን ይህ ሲደረግ ጥራትን ለማስጠበቅ ሲባል ከመጠን በላይ ወጪ በምርቱ ላይ ወጥቶ ካለን የማምረት ልምድ፣ ካለን ማሽነሪ እንዲሁም ካለን የሰው ኃይል ጋር ሲደማመር ዋጋውን ከፍ ሊያደርገው ይችላልና ጥንቃቄ የሚያሻው መሆኑን ያመለክታሉ። ጥራቱን ጠብቆ ዋጋውም ለተወዳዳሪነት በሚያበቃ መልኩ ማምረት ከተቻለ ግን መልካም እድል መሆኑን ያስረዳሉ።

ቻይና የሰጠችው እድል በጣም ትልቅ እድል ነው ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፣ ኢትዮጵያ አሁንም ቢሆን ከአግዋ በስተቀር የገበያ እድል እንዳላት ግን አልሸሸጉም። ኢትዮጵያ ከጦር መሳሪያ በስተቀር ሌላውን ምርት በነጻ ታስገባለች የሚል ስምምነት ላይ የተደረሰበት የአውሮፓ የገበያ እድል (Everything but Arms) (EBA) አለ በማለት ማሳያ አስቀምጠዋል።

ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ የጦር መሳሪያ አምርታ የምትሸጥበት ጊዜ ላይ ስላልሆነች ከጦር መሳሪያ ውጪ ሁሉንም ምርት ወደእዛ ማስገባት ትችላለች ማለት ነው ይላሉ። እንዲህም ሲባል ችግር የለም ማለት አይደለም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የምትልካቸው ምርቶች ሁሉ የራሳቸውን መስፈርት ካላሟሉ መከልከላቸው አይቀርም ባይ ናቸው። ለምሳሌ ጥራታቸውን ካለመጠበቅ የተነሳ በቀላሉ የአውሮፓንም ሆነ የቻይናን ገበያ መቆጣጠር አይችሉም። ለምሳሌ የሚላኩ ምርቶች ምግብ ነክ ከሆኑ በጤና ላይ የሚያደርሱት እክል ሊኖር ይችላል። ስለዚህ ጥራታቸውን የጠበቁና ደረጃቸውን ያሟሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ለምሳሌ አንዱን ምርት ብቻ ወስደን ለማየት ብንሞክር ስጋ ብንልክ በጣም ከፍተኛ ጥቅም እናገኛለን። በዚህ ዘርፍ እነ ኬንያ አብዝተው ይጠቀማሉ ሲሉ ሁኔታውን ያመለክታሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አምባሳደር እንደሚሉት፣ በኢትዮጵያ በኩል ስጋ ለመላክ የሚያስችል አቅም ቢኖረንም ከጥራት ጉድለት የተነሳ ማግኘት የሚገባንን ጥቅም ማግኘት አልቻልንም። በተለይም ያሉንን ከብቶች በሽታ ስለሚያጠቃቸው በሽታ በመከላከል ላይ አልሠራንም። የኢትዮጵያ መንግስት ከብት እርባታ ላይ ለመስራት ተነሳሽነቱ እንዳለውና በትኩረት እንደሚሰራም ይናገራል። ነገር ግን በሽታን ከማጥፋት ጋር የተሰራው ነገር በቂ አይደለም።

ለዚህም ዋና ምክንያት ከተባለ አንድ አርሶ አደር በዓመት ከበሽታ የተነሳ አራት ያህል ከብት እንዲሚሞትበት ሲናገር መደመጡ ነው። እንዲህ አይነቱ በሽታ እና ችግር እስካለ ድረስ ስጋ ወደ አውሮፓ ገበያ መላክ አንችልም። ይህ ችግር እስካልተፈታ ድረስ ደግሞ ወደቻይናም ለመላክ ያስቸግራል ሲሉ አምባሳደሩ ያስረዳሉ።

ስለዚህ ይላሉ አምባሳደሩ፣ ከቀረጥ ነጻ እድል ቢገኝም ከሌሎች ችግሮች ማለትም ጤና እና ጤና ነክ የሆኑ ችግሮችን ከሚፈጥሩ ነገሮች መጠበቅና ችግሩን ማሻሻል የግድ ይላል። ምክንያቱም ከጥራት ጉድለት ጋር ተያይዞ የሚመጣው እንከን ሸቀጣችንን ማገዱ አይቀርም። በዚህ ችግር ምክንያት ከምንጠቀመው እድል እንዳንስተጓጎል በትኩረት መስራትን ይጠይቃል። የአውሮፓን እድል የነሳሁበት ምክንያት ቀደም ሲል የተሰጠውን እድል አሟጥጠን መጠቀም ያልቻልንበት ምክንያት ጥራት መሆኑን ለማሳየት ይረዳኛ ዘንድ ነው ብለዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ አቶ ሞገስ ደግሞ በሌላ በኩል፣ መታየት ያለበት ጉዳይ አለ ይላሉ። እርሳቸው አንድ ምርት ሲመረት የወጣበትን ወጪ አስልቶ ወደቻይና ማጓጓዝ ምን ያህል ትርፋማ ነው የሚለው መለካት አለበት ባይ ናቸው። የውጪ ገበያ እድል ብቻ ስለተገኘና የውጭ ምንዛሬ ስለሚፈለግ ብቻ በብዙ ድጎማዎች አዋጭ ሳይሆኑ እንዲሁ የሚገባበት ጊዜ ነበር። ለምሳሌ ወደ ኤክስፖርቱ ዘርፍ የሚገቡ ድርጅቶች ወይም አምራቾች ከኢትዮጵያ መንግስት ብዙ ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ። እሱ ሲደመርበትና እዛ የተላከበት ሀገር የሚሸጥበት ዋጋ ሲነጻጸር ሽያጩ ኪሳራ ነው ማለት ያስደፍራል ሲሉ እውነታውን ያሳያሉ።

አቶ ሞገስ፣ ለዚህ አባባላቸው በምክንያትነት የጠቀሱት፣ እዚህ የሚደረግላቸው ጥቅማጥቅሞች ለምሳሌ ጥሬ እቃ ሲያስገቡ ግብር አለመክፈል ይሆናል፤ ይህንና መሰል ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ። ይህ ሁሉ ወጪ ተደማምሮ ምርቱ ዋጋ የሚያወጣ ከሆነ አዋጭ ነው ማለት ይቻላል ብለዋል።

ሌላው በቻይና ያሉ ድርጅቶች በሀገራቸውም ሆነ ከሀገራቸው ውጪ በጣም ተወዳዳሪ ናቸው። ወደ እኛዎቹ ሲመጣ የዚያን ያህል በሀገር ውስጥ ውድድር የለም። ውጪ ሲሄዱ ደግሞ የሚገጥማቸው ውድድር በጣም ከፍተኛ ነው። ቻይና ደግሞ እድሉን የምትሰጠው ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካ ሀገሮችም ጭምር ነው። ስለዚህ ውድድሩ በእኛና በእነዛ የአፍሪካ ሀገራት መካከል ይሆናል። ስለዚህ የእነርሱንም ውድድር በአግባቡ ለመወጣት መስራትና መከታተል ያስፈልጋል። በተለይም የተሻለ ልምድ የሚኖራቸውም ከሆነ ከእነርሱ መውሰድ መልካም መሆኑን አስገንዝበዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት የተፈቀደላትን ምርት በጥራት የማቅረብ ቁመና ላይ ናት ማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም መሟላት የሚገባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል ምርትን በአግባቡ ለማምረት የሙብራት መቆራረጥ መኖር የለበትም። ይህ ችግር ደግሞ አሁንም ያልተፈታ ነው። ውሃም እንዲሁ ነው። ስለዚህ ከእነዚህ ሁሉ ችግሮች ወጥተን በአንድ ግብ ለአንድ ዓላማ መስራት ያስፈልጋል። ቁመናችን በዚህ ልክ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ኤክስፖርታችን ከጊዜ ወደጊዜ እየወረደ አይመጣም ነበር። እስካሁንም እያገኘን ያለነው ከብዛት እንጂ ከጥራት አይደለም።

ቻይና ምርቶቿን በሀገራችን በዝቅተኛ ዋጋ ታቀርባለች፤ ለምሳሌ ብረታብረትን መውሰድ ይቻላል። ስለዚህ እኛ በምናመርተው ምርት እዚሁ ሀገራችን ውስጥ እንኳ መወዳደር አንችልም። ቻይናም ይዛ የምትመጣው ምርት ይኖራልና ለእዛም መዘጋጀት ያስፈልጋል ሲሉ አስገንዝበዋል። ከአሁን በፊት ሚዛኑ የሚደፋው ወደ እነርሱ ነው። ከአፍሪካ ጋር ለሚደረገውም የንግድ ልውውጥ ዝግጅት ያስፈልጋል ባይ ናቸው። በቅርቡ በመዲናችን የተካሄደው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ ላይ የአፍሪካ ሕብረት ውሳኔ አንዱ ይህ ነውና ብለዋል።

ቻይና ቀደም ሲል ኢትዮጵያ 1 ሺ 644 ምርቶች ከቀረጥ እና ኮታ ነጻ ማስገባት እንደምትችል ፈቃዱን ያሳወቀችው ታኅሣሥ 3 ቀን 2015 ዓ.ም. መሆኑ የሚታወስ ነው። የአሁኑ የተሰጠው እድል ደግሞ ተጨማሪ የተሰጠ ነው።

አሜሪካ የአፍሪካ ሀገራት ከቀረጥ ነጻ ወደግዛቷ እንዲያስገቡ ከፈቀደችው የአጎዋ እድል ኢትዮጵያን በጥቅምት ወር 2014 ዓ.ም ላይ በፕሬዚዳንቷ አማካይነት መሰረዟ የሚታወስ ሲሆን፣ በወቅቱም የኢፌዴሪ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአሜሪካ መንግስት ውሳኔ የተደረሰው ክልከላ እንዳሳዘነው በወቅቱ ማሳወቁ ይታወሳል።

አቶ ሞገስ፣ የቁጥጥር ባላስልጣኑ ወደውጭ በሚሄዱ ምርቶች ላይ በቅርበት ክትትል ማድረጉን ከሌላው ጊዜ በተሻለ መልኩ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል ይላሉ። በሁለትና በሶስት አምራቾች ብቻ የወጪ ገበያውን እድል መጠቀም ውጤት አያመጣምና በዚህ ዙሪያ መንግስት በትኩረት ተከታትሎ የተፈለገውን ውጤት ለማምጣት መስራት ይጠበቅበታል ብለዋል።

አምባሳደር ጥሩነህ፣ ጥራትን ለማምጣት መስራት እንችላለን ይህ የማይቻል ነገር አይደለም፤ ይህ ፊዝክስ አይደለም፤ ይሁንና አልሠራንም። ትኩረት አድርገን ብንሠራና የእንስሳት በሽታን ለማስወገድ ብንችል ከእንስሳት ሀብታችንም ልናገኝ የምንችለው ጥቅም በጣም ከፍተኛ ነው። እንስሳትን በተመለከተ በሽታው ላይ ከመስራት በዘለለ ደግሞ በዝርያ ማሻሻልና አያያዝ ላይም እንዲሁ መስራት ይኖርበታል። መንግስት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ በአሁኑ ወቅት ከበፊቱ ይልቅ የተሻለ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም አርሶ አደሩ ምርቱን እንዲያሻሽል ከወትሮ በተሻለ መንቀሳቀስ የግድ እንደሚል ጠቅሰው፣ 60 በመቶ ያህሉ መሬት በደንብ አልታረሰምና ያለውን መሬትም ለመጠቀም መታተር ብሎም ለአርሶ አደሩ ቴክኖሎጂውን ማቅረብ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። አርሶ አደሩ ያመረተውንም ምርት ሳይበላሽ የሚያቆይበትን መሳሪያ ማበጀት አስፈላጊነቱን አስረድተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የሴቶች ቀንና የወንዶች አጋርነት

**ሰላማዊት ውቤ**

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ እና በማህበራዊ መስኩ ከወንዶች እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል በየዓመቱ ይከበራል። ጾታዊ ጥቃትን ለማስቆምና የህግና የሰብዓዊ መብታቸውንና ነፃነታቸውን ለማስከበር ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ቆይቷል። ለዚሁ ዓላማ ትግል ያደረጉ ሴቶችን በመዘከር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እ.ኤ.አ በ 1975 በይፋ ሲያከብረው ዓለማቀፋዊ ይዘቱ የተጠናከረው በዓሉ እ.ኤ.አ ከ1911 ጀምሮ እንደሆነ ይገለጻል።

ታዲያ ዘንድሮ ይህ በዓል በዓለም ለ110ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ47ኛ ጊዜ ይከበራል። ለምን ይከበራል ከተባለ ደግሞ ቀድሞ ዓላማን ማወቅ ከምንም በላይ ያስፈልጋል። በሴቶች ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሙና አህመድ ስለዚሁ ዓላማ እንዲህ ሲሉ ያብራራሉ።

የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በዓሉ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የተደረገ ትግልን መሰረት አድርጎ የተጀመረ ነው። መነሻው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1908 በኒውዮርክ ከተማ ነዋሪ የሆኑ 15 ሺህ ሴቶች ሲሆኑ፤ የተነሱበት አላማም የተሻሻለ የሥራ ሰዓትና የደመወዝ ክፍያን እንዲሁም የመምረጥ መብታቸው እንዲከበር መጠየቅን ያለመ ነው። አደባባይ በመውጣት ሀሳባቸውን አስተጋብተዋል።

ዓላማው ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ እና በማህበራዊ መስኩ እንዲሁም በጋራ የሀገር ግንባታ ላይ ከወንዶች እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ታሪካዊ ቀን ሆኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ መከበር የጀመረው በአውስትራሊያ፣ ዴንማርክ፣ ስዊድንና ጀርመን እ.ኤ.አ በ1911 ነው። ስያሜውን ያሰጠችውም በዴንማርክ ዋና ከተማ ኮፐንሀገን በተካሄደ ሁለተኛው የሴቶች ኮንፈረንስ የተገኘችው ክላራ ዜትኪን የተሰኘች ጀርመናዊት ሴት ነች። ይሄን ተከትሎም ቀኑ ዛሬ ድረስ በዓለም ላይ የሚገኙ ሴቶች ዘር፣ ቀለም ፣ቋንቋ ፣ሃይማኖት እንዲሁም መልካ-ምድራዊ ድንበር ሳይገድባቸው ሕብረት ፈጥረው ለነጻነታቸው፣ ለሰብዓዊ እኩልነታቸው፣ ለፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው መረጋገጥ በአንድነት እንዲያከብሩት ሆነዋል። ድምፃቸውን እያሰሙበትም ቀጥለዋል።

እንደ ሀገርም ባለፉት ዓመታት በዓሉን ይሄን መሰረት አድርጎ ነበር ሲከበር የቆየው ያሉት ወይዘሮ ሙና፤ በ2013 ዓ.ም ወሩን ሙሉ በተለያየ መርሃ ግብር በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር ቆይቷል። ወሩን ሙሉ በተለየ ሁኔታ ለማክበር በፌዴራልም በክልሎችም የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል። ‹‹ወሩን ሙሉ ሲባል ወሩን ሙሉ ለሴቶች መብት ትኩረት ተሰጥቶ ተሰርቷል›› ማለት ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ‹‹የሴቶችን መብት የሚያከብር ማህበረሰብ እንገንባ›› የሚል መሪ ሀሳብ በመያዝም ነበር የተከበረው። ጥሩ መነቃቃት የፈጠረ እንደነበርም ታይቷል በማለት ያስታውሳሉ።

መሪ ሀሳቡ ‹‹የሴቶችን መብት የሚያከብር ማህበረሰብ እንገንባ›› እንደመሆኑ ከምንም በላይ የማህበረሰቡን ለሴቶች ያለውን የተዛባ አመለካከት የሚቀይር ሥራ መሥራት አለብን የሚለውን የሚያመለክት ነው። ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በየደረጃው ሁሌ ስለ ሴቶች መብት እኩል እንዲናገር ማስቻል ይኖርብናል ብለን ሰርተናል ይላሉ።

‹‹ወሩን ሙሉ አልኩ እንጂ በዓሉ ዓመቱን ጠብቀን አንድ ቀን ብቻ የምናከብረው አለመሆኑ ግንዛቤ ሊያያዝበት እንደሚገባ መናገር እፈልጋለሁ›› ብለዋል ሚኒስትር ዴኤታዋ። እንዳከሉት በዓሉን እስከ አሁን በነበረው ሂደት ሁልጊዜ ቀኑን ጠብቀን አንድ ቀን ብቻ ነበር የምናከብረው። አሁን ላይ ቆም ተብሎ ሲታሰብ ታዲያ ለሴት ስለመብቷ አንድ ቀን ብቻ ማውራት ትክክል አይደለም። ዓመቱን ሙሉ ልናወራላትና ዓመቱን ሙሉ የሴቷን መብት እያከበርን መሄዳችንን ማረጋገጥ አለብን የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። በዚህም በዓሉ መከበር ያለበት አግባብ ትኩረት ተችሮት ነው። ይህንንም እያስፈጸምን እንገኛለን።

እንደ ሚኒስቴር ዴኤታዋ ማብራሪያ፤ አንዱን



የወጣቶች ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ ወይዘሮ ሙና አህመድ

ወርም ቢሆን ትኩረት እንዲሰጠው ተደረገ እንጂ ዓመቱን ሙሉ የሴቶችን መብት ማክበር አስፈላጊ ነው። ይሄ በየደረጃው ታሳቢ መደረግ አለበት። እንዴት ነው የሴቷን መብት እያከበርን ያለ ነው በማለት ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጆች ምን ያህል የሴቶችን መብት እያከበሩ ነው ያሉት፣ የሕግ ማዕቀፎች ምን ያህል እየተተገበሩ ነው? የሚለውን መፈተሽ፣ ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግና ምላሽ ማግኘቱንም ማረጋገጥ ይገባል።

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ደረጃ በተለይ በኮቪድና የተለያዩ ግጭቶች በተፈጠሩበት ወቅት ሴቶችና ህፃናቶች የጥቃት ሰለባ የሆኑበት እንዳለ በመስክ ምልከታ የተደገፈ መረጃ ነበር። በቀጣይ ሴቶች ለእዚህ ዓይነቱ ድርጊት እንዳይጋለጡ መታደግ የሚያስችል ሥራ በስፋት ተከናውኗል። ይሄ ሲሰራ ከጾታዊ ጥቃት ጋር ተያይዞ ታክስ ፎርስ ነበር። ይሄ ሴቶች፣ ጠቅላይ ዓቃቢ ህግ፣ ጤና ተቀናጅተው ሲሰሩት የቆዩት ነበር። በተጨማሪም ይሄን መሰረት አድርጎ እንደ ተቋም ጾታዊ ጥቃትን ከመከላከል አኳያ ‹ብሔራዊ የጾታዊ ጥቃት ወንጀል› የመረጃ ስርዓት እየተዘረጋ የነበረበት እንደነበርም ያወሳሉ። ለዚህ የሰነድ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። በቀጣይ ከሚመለከታቸው የተቋማት ኃላፊዎች ጋር ተፈራርሞ ወደ ሥራ የመግባቱ ጉዳይ ለመተግበር ዝግጅት ተደርጎም ነበር። እንደውም ይሄ ሥራ ትልቅና እንደ ሀገር የመጀመሪያውም ነበር። ዋናው ዓላማው ጥቃት አድራሾች መረጃቸው በትክክል እንዲያዝ ማስቻል ሲሆን ይሄ ወንጀልን ከመከላከል አኳያ ሕብረተሰቡንም ለማስተማር በእጅጉ የሚረዳ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል። አጥቂዎች ዳግም ጥቃት እንዳይፈፅሙ ለማድረግም አስተዋጽኦ የጎላ እንደሆነ ታሳቢ ተደርጎ ነው ወደ ሥራ ተገብቶ የነበረው።

በዚህ በ2013 ዓ.ም ከጾታዊ ጥቃት መከላከል ጋር ተያይዞ ትልቁ ችግር መረጃ የነበረ ሲሆን ተግባሩ እንደ አንድ የመረጃ ምንጭ በመጠቀም ወንጀሉን መከላከል እንደሚያስችልም ታምኖበት ነበር።

የጥቃቱ ወንጀል መንስኤ ምንድነው ከተባለ የመጀመሪያው በህብረተሰብ ውስጥ ለሴቶች ያለ የተዛባና ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአመለካከት ችግር፣ የወንዶች የበላይነት መስፈን፣ አንዳንድ ሴቶች ለራሳቸው ያላቸው አመለካከት ዝቅ ማለት ወይም በራስ መተማመን መጥፋት፣ የሕግ አተገባበርና የአፈፃፀም ችግር ነው። ሌላውና ራሱን የቻለ መንስኤ በ1985 የወጣው የሴቶች ፖሊሲ ነው። ይሄ ማለት ህገ መንግስቱና የሴቶች ፖሊሲ አይጣጣሙም ማለት ነው። ፖሊሲው ብዙ ነገሮች ይጎሉታል።

እንደ ተቋም ጉድለቱን የመሙላቱ ሥራ ተጀምሯል ያሉት ሚኒስቴር ዴኤታዋ፤ በድጋሚ እየተከለሰ ያለበት ሁኔታ አለ። አቅጣጫ የማስቀመጥና ክፍተቱን የመፈተሽ፣ የወጡ ህጎችንም እንዴት ነው ተግባራዊ እየሆኑ ያሉት በማለት በደንብ ተዟዙሮ ማየት ያሻል። አሁን ያለው ዓለም የወንዶች የበላይነት ያለበት ነው። ከዚህ አንፃር አንዳንድ የወንድ ሀሳብን ሴቶች የሚጋሩበት ሁኔታ ስለሚታይ እዚህ ላይ በሚገባ መሥራት ያስፈልጋል።

እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚ እንሁን ስንል የመብትም ጉዳይ ነው። የመብት ጥያቄያችን በዚህ ደረጃ ነው ወይ የሚታየው የሚለው ሥራ ይፈልጋል። በመሆኑም አስተሳሰብ ላይ በየደረጃው መሥራት ይጠይቃል። በዚህ በኩል ሁሉም መገናኛ ብዙሃን ሊሰሩበት ይገባል። ሴቶች በአመራርነትና ውሳኔ ሰጪነት ደረጃ መምጣት አለባቸው የሚለው ከመብትም አኳያ መታየት አለበት።

‹‹ወንዶች ሰጪ እኛ ተቀባይ መሆን የለብንም የሚል ዕምነት አለኝ።›› የሚሉት ወይዘሮ ሙና፤ ይህ ጉዳይ መብታችን ነው! ዕድሉን ብናመቻችላቸው፣ ብንደግፋቸው ብናበቃቸው በእርግጠኝነት ነገ የሀገር መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ሴቶች ማየት እንችላለን። በዚህ ረገድ የተጀመሩ ሥራዎች አሉ። ሆኖም ደጋግሞ ወደ ታች እያወረድን ስንሄድ ዝቅ እያለ የሚሄድበትን በሚገባ ማየት ያስፈልጋል ሲሉ ያብራራሉ።

ወረዳ ላይ በአስፈፃሚነት ያሉ ሴቶች 25 ነጥብ 9 ናቸው። በፌዴራል ደረጃ ያለው 50 በመቶ የሴቶች ተሳትፎ እንዳይቀንስ ሥራዎችን ተቀናጅቶ መሥራት ይፈልጋል። በስተኋላ ላይ ቀድመን ያልዘራነውን ማጨድ ስለማንችል ዛሬ ሴቶችን ማብቃት፣ ዕድሎችን ማመቻቸት ይገባል። ሴቶች ሁኔታዎች ስላላመቻቸንላቸውና ዕድል ስላልሰጠናቸው ነው እንጂ ይችላሉ። አሁን ላይ እጅግ ጠንካራ ነገ ሀገር መምራት የምትችል ሴት እያየን ነው። በቀጣይም በዚህ ደረጃ ውጤት የሚያመጣ ሥራ መሥራት አለብን ሲሉ አሳስበዋል።

በዚህ ዙሪያ እንደ ተቋም ያቀድናቸው ዕቅዶች አሉ። በተለይ ትምህርት ቤቶች አካባቢ ያሉ ታዳጊ ሴቶች አርአያ የሚሆናቸው ይፈልጋሉ። ከዚህ አንፃር የተጀመረ መርሐ ግብር አለ። በቀጣይ ሰፍቶ የሚሄድበት ሁኔታም ተመቻችቷል ብለዋል።

የሴቶች ጥያቄ የመብት ጥያቄ ነው፣ የተሳትፎ ጥያቄ ነው፣ የተጠቃሚነት ጥያቄ ነው። ጥያቄዎቹን ነጣጥለን ማየት የለብንም። የመብት ጥያቄ ስለመለሰን ሌላው አብሮ ተመልሷል ተብሎ የሚተው አይደለም። የሴቶች እኩልነት መብት ጥያቄን ካረጋገጥን ሀብት ምንጮች ላይ መጠቀም መብት ያገኛሉ። ኢኮኖሚያቸውንም ያሳድጋሉ። ይህ ሆነ ማለት ደግሞ የማህበራዊ ችግሮቻቸውን እየፈቱ ይሄዳሉ። በመሆኑም የሴቶችን ጥያቄ ነጣጥለን መመለስ የለብንም ይላሉ።

የሴቶችን ጥያቄ አስተሳስሮ ካልተመለሰ ክፍተት ስለሚፈጠር የማህበራዊ ተጠቃሚነቷን በመመለሳችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቷ ተመለሰ ማለት አይቻልም። የመብት ጥያቄዋም እንዲሁ ተመለሰ ማለት አይቻልም። በመሆኑም እነዚህን ሳንነጣጥል አብረን አስተሳስረን ልንመልስ ይገባል። ይሄን ለማድረግ በሴቶች መዋቅር የሚሰራው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው ያለው አመራር በያለበት ለሴቷ ጠብ የሚል ነገር መሥራት አለበት። የሚደነቁ ጅምሮች ቢኖሩም አሁን ድረስ ሴቶች በፖለቲካውም፣ በኢኮኖሚያዊውም ሆነ በማህበራዊ መስኩ ተጠቃሚ ነን የሚል የለም። በመሆኑም ጅምሮቹን አጠናክረን ክፍተቶቹን ሞልተን ለመጪው ትውልድ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንችላለን። ይሄንን ለማድረግ ደግሞ በየደረጃው ያለውን አካላት ትብብር ይፈልጋል ባይ ናቸው።

በምሳሌነት የሚያነሱት ደግሞ የወንዶች አጋርነትን ነው። አሁንም የሴቶች ጥቃት አልቆመም። በመሆኑም ከምን ጊዜውም በላይ የወንዶች አጋርነት እጅግ ያስፈልጋል። ችግሩን ከምንጩ ልናደርቀው ከሆነ ወንዶችን ማሳተፍ የበለጠ ጠቃሚ ነው። ሰጪና ተቀባይ ዓይነት ሳይሆን እኩል ዕድል ሊፈጠርልን እንደሚገባ መረዳት አለባቸው። የጋራ ሀገር እስካለን ድረስ በሀገረ መንግስት ግንባታ ላይ እኩል መሳተፍ እንዳለብን ማወቅ አለባቸው።

ሴቶች ደካማ ስለሆን ሳይሆን ከታች ይዘን የመጣናቸው ችግሮችና ድርብ ኃላፊነቶች አሉብን። ሴቷና ወንዱ በቤት ውስጥ እኩል አይደለንም። እኛ የቢሮም ሥራ እንሰራለን። እቤትም ስንገባ ልጆችና ቤተሰብ ከመንከባከብ ጀምሮ የቤት ውስጥ ሥራ ይጠብቀናል። የገጠር ሴቶች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በቤት ውስጥ ሥራ ነው። በዚህ ላይ የተደረጉ አንዳንድ ጥናቶች ሲያይዋቸው የኢትዮጵያ ሴቶች ስንት ሰዓት ነው የሚሰሩት? ይላሉ። በመሆኑም ወንዱ በቤት ውስጥ ይሄን ጫናዋን የሚቀንሱ ቴክኖሎጂዎችን እንድትጠቀም በማድረግ ሊያግዛት ይገባል።

ሴቶች በዚህ ውስጥ አልፈው ነው ከፍተኛ ስልጣን ላይ ሆነው ሀገራቸውን እየመሩ የሚገኙት። መምራት ታች ከቤተሰብ ከማስተዳደር እንደመጀመሩ እየተለማመድነው ነው የመጣነው። በግሌ ሴቶችን ወደ አመራርነት የሚያመጣ መንግስት ወይም መሪ እጅግ የገባው ነው ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም ወንዶች ታማኝ አይደሉም እያልኩ ሳይሆን ሴት የበለጠ ታማኝ ነች። አንድ የቤት ሥራ ከተሰጣት የቤት ሥራው ሳይበላሽ ከግብ እንዲደርስ ትጥራለች። ይሄ ምን ያህል ኃላፊነት የሚሰማት እንደሆነች ነው የሚያሳየው። ከዚህ አንፃር ለሴቶች የወንድ አጋርነት ያስፈልጋል ሲሉም ያብራራሉ። አዎ ወንድ ያለ ሴት እንደማይቆም ሁሉ ሴትም ያለወንድ ውጤታማ ልትሆን አትችልም። ስለሆነም አጋርነታቸውን በስፋት ሊያሳዩዋት ይገባል በማለት ሀሳባችንን ቋጨን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በ1960ዎቹ ከታተሙ የአዲስ ዘመን ጋዜጦች ላይ ለንባብ ከበቁ አንዳንድ ዘገባዎች መካከል ለዛሬ የተወሰኑትን ለማስታወስ መርጠናል፡፡ከመረጥናቸው ዘገባዎች መካከል አብዛኞቹ በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ዛሬ ላይ ስንመለከታቸው ግርምት ይፈጥራሉ ብለን ያሰብናቸውን ዘገባዎችም ቀነጫጭበን እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል፡፡

### ዝንጀሮዎች ሰው ገደሉ

ጐፋ፤ (ኢ-ወ-ም) በገሙ ጐፋ ጠቅላይ ግዛት በጐፋ አውራጃ በጐፋ ወረዳ ኮስቲ በተባለው ቀበሌ ሺበሺ ሴንሣ የተባለው የ፲፪ ዓመት ልጅ የበቆሎ ሰብል ሲጠብቅ ዝንጀሮዎች በቆሎውን ለመብላት መጥተው ሊያባርራቸው ቢሞክር ተሰብስበው በመያዝ እየጐተቱ የገደሉት መሆኑን የአውራጃው ፖሊስ አዛዥ በጽሑፍ መግለጣቸውን ዋናው ጸሐፊ አቶ ታደሰ ለገሠ አስታወቁ፡፡(መስከረም 9 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

### ባለ የ158 ዓመት ዕድሜ ሰው በኬንያ ተገኙ

ከናይሮቢ ፤(ኤ-ኤፍ-ፒ) ዕድሜዬ ፩፻፶፰ ዓመታት ነው፡፡እ/ኤ/አ/ በ፲፰፻፶፱ ዓ/ም/ ወደ አፍሪካ ከመጡት ከሊቪንግስተን ከሌሎችም ተጓዦች ጋር ተገናኝቻለሁ የሚሉ አንድ ኬንያዊ ገበሬ በአሁኑ ጊዜ ባላቸው አሥር ጋሻ መሬት ላይ የተለመደ ሥራቸውን ሲያከናውኑ ይገኛሉ፡፡

በናይሮቢ አቅራቢያ የሚገኙት ሳምሶን ሻኩራጎ፤ በአሁኑ ጊዜ በምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ከሚገኙት ብዙ ዓመታት የኖሩ ሰዎች ሁሉ የሚበልጡ አንጋፋ ናቸው፡፡

በታንዛኒያ ውስጥ ዓይናቸውን ተቀድደው ሕክምና ሲደረግላቸው ከቆዩ በኋላ በቅርቡ የተደረገላቸው ምርመራ እንደሚያመለክተው ዓይናቸው ድኗል፡፡

የርሳቸውም አባት የናስላንድ ጐሣ ባላባት ነበሩ። ከነበሩዋቸው ፴፱ ሚስቶች ፩፻፴፩ ሴት ልጆችና ፶፰ ወንዶች አስወልደዋል፡፡ከእነዚህ መካከል ፩፻፶፰ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሻኩራጎ የመጀመሪያ ልጅ ናቸው፡፡

ሻኩራጎ እ/ኤ/አ/ በ፲፰፻፺፯ ዓ/ም/ ተጠምቀው ፕሮቴስታንት እስከሆኑ ድረስ ሦስት ሚስቶች እና 16 ልጆች ነበራቸው፡፡ነገር ግን ፕሮቴስታንት ከሆኑ በኋላ ሁለቱን ሚስቶቻቸውን ፈተው በአንድ ተወስነው ሲኖሩ እ/ኤ/አ/ በ፲፱፻፳ ዓ/ም/ ሚስታቸው በመሞታቸው እ/ኤ/አ/ በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም በ፩፻፳፩ ዓመታቸው አራተኛ ሚስት አግብተው አራት ሕፃናት አስወልደዋል፡፡ አራተኛዋ ሚስታቸውም በወሊስ ሞተዋል፡፡

(መስከረም 17 ቀን 19 60 ከታተመው አዲስ ዘመን)

### ልጅዋን በሆስፒታል ጥላ ጠፋች

አዲስ አበባ ፤(ኢ-ዜ-አ) ፤ አንዲት ሴት የሶስት ወር ሕፃን ከፓርላሜንት አካባቢ ይዛ ወደ ልዕልት ፀሐይ ሆስፒታል ከወሰደች በኋላ ፤ርዳታ ያደረገላትን የቀን ሠራተኛ ‹‹ሕፃኗን የማሳክምበት ካርድ እስካወጣ ይዘህልኝ ጠብቀኝ ›› በማለት ሕፃኗን ጥላ መሔዷን የአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አስታወቀ፡፡

ሴትየዋ ይህቺን የሦስት ወር ሕፃን ወደ ሆስፒታሉ የወሰደችው ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ ነው፡፡በዚህ ጊዜ ርዳታ ያደረገላት አቶ ታምራት በላይ የተባለ የቀን ሠራተኛ ሲሆን ፤ሁኔታውን ለማወቅ የተቻለው እርሱ በሰጠው ቃል መሰረት መሆኑን የአምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ የምርመራ ክፍል ሹም ጥላሁን ዓሊ አስረድተዋል፡፡ ሕፃንዋ ለመጀመሪያ ጊዜ አስፈላጊው ሕክምና ከተደረገላት በኋላ ፤ የሆስፒታሉ ኣላፊዎች ወደ አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ እንድትወሰድ ያደረጉ መሆናቸውን የዚሁ ጣቢያ የምርመራ ክፍል ሹም በተጨማሪ ገልጠዋል፡፡

(መስከረም 27 ቀን 19 60 ከታተመው አዲስ ዘመን)

### ፍየሏ ፤ በግና ፍየል በአንድ ጊዜ ወለደች

ጐንደር፤(ኢ-ዜ-አ) በቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት በጐንደር አውራጃ ዘንጋጅ ምክትል ወረዳ ግዛት ውስጥ አንዲት ፍየል አንድ በግና አንዲት ሴት ፍየል ባንድነት ወለደች፡፡

በአንድነት የተወለዱት በግና ፍየል ግልገሎች ሁለቱም የሚገኙ መሆናቸውን የጐንደር አውራጃ ገዢ ፊታውራሪ ተስፋ አስናቀ ገለጡ፡፡

ፍየሊቱ በዘንጋጅ ምክትል ወረዳ ነዋሪ የሆኑት የአቶ ጫሉ ገሠሠ መሆናቸው ታውቋል፡፡

(መስከረም 27 ቀን 19 60 ከታተመው አዲስ ዘመን)

### የዓቢያታና ሻላ ሐይቆች ለዓሣ ማጥመድ ሥራ ተከለከሉ

አዲስ አበባ ፤(ኢ.ዜ.አ) በስምጥ ሸለቆ (ሪፍጥ ቫሌይ) ውስጥ በሚገኘው ብሔራዊ ክልል ያሉት የዓቢታና ሻላ ሐይቆች ለዓሣ ማጥመድ ተግባር የተከለከሉ መሆናቸውን የዱር አራዊት ጥበቃ ትናንት አስታወቀ፡፡

በተጠቀሱት ሐይቆች አካባቢ በዓለም ውስጥ ሊጠፉ የተቃረቡ ፤እንዲሁም በዓለም የማይገኙ ፤ቱሪስትን ለመሳብ የሚችሉ ልዩ ልዩ ብርቅ አእዋፋት አካባቢ በዓለም ውስጥ ሊጠፉ የተቃረቡ ፤እንዲሁም በዓለም የማይገኙ፤ ቱሪስትን ለመሳብ የሚችሉ ልዩ ልዩ ብርቅ አእዋፋት እነዚህኑ አእዋፋት ለማየትና ጥናት ለማድረግ ከተለያዩ አገሮች የሚመጡ ፊልም አንሺዎችና የተፈጥሮ ጥናት ተመራማሪዎች ቁጥር እየጨመረ መሔዱን ድርጅቱ ጠቅሶ ፤አእዋፋቱ ሁለቱ ሐይቆች የሚያፈሩትን ዓሣዎች በመመገብ የማይኖሩ በመሆናቸው ዓሣ ማጥመድ የተከለከለ መሆኑን አስረድቷል፡፡

በዚህም ምክንያት የስምጥ ሸለቆ ብሔራዊ ክልል ሆነው በሚገኙት ዓቢታና ሻላ ሐይቆች ውስጥ ገብቶ ዓሣ ማጥመድ እንደማይፈቀድና በሁለቱ ሐይቆች ውስጥ የሚገኘው የዓሣ ምርት ‹‹የተፈጥሮ ፀጋ›› ለሆኑት አእዋፋት መኖ መሰጠቱን ድርጅቱ አስታውቋል፡፡

በተጠቀሱት ሐይቆች ማኛውም ሰው የዓሣ ማጥመድ ሕግን በመጣስ እንዳያከናውን ድርጅቱ አሳስቧል፡፡

(የካቲት 23 ቀን 1965 ከታተመው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ



## ደቡብ ሱዳን የመከላከያ እና የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሮችን ከኃላፊነት አነሳች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር የሀገሪቱ መከላከያ እና የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሮችን ከኃላፊነታቸው አነሱ፡፡

ደቡብ ሱዳን በዲሞክራሲያዊ ምርጫ የተመረጠ መንግስት እስኪቋቋም ድረስ በስልጣን ላይ ያለው የሽግግር መንግስት በታኅሳስ 20 ቀን 2024 ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ በስልጣን ላይ ይቆያል መባሉ አይዘነጋም፡፡

ይሁን እንጂ የደቡብ ሱዳን ፕሬዝዳንት ሳልቫ ኪር ከተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ሪክ ማቻር ጋር የተፈራረሙትን የሰላም ስምምነት የሚጻረር እርምጃ መውሰዳቸው እየተነገረ ነው፡፡

ሳልቫ ኪር የመከላከያ እና የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትሮችን ከስልጣናቸው ያባረሩ ሲሆን ውሳኔው በሀገሪቱ ሰላም ለማምጣት የተደረሰውን "የሰላም ስምምነት የሚጥስ ነው" ተብሏል፡፡

ከስልጣን የተባረሩት የመከላከያ ሚኒስትር አንጀሊና ቴኒ የማቻር ባለቤት ሲሆኑ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ ደግሞ ማህሙድ ሰለሞን ናቸው።

ሮይተርስ እንደዘገበው ፕሬዝዳንት ኪር የሰላም ስምምነቱን የጣሱት በስምምነቱ መሰረት የማቻር ፓርቲ የተሰጠውን የመከላከያ ሚኒስቴር ኃላፊነት ወደ ፓርቲያቸው እንዲሁም በምትኩ የፓርቲያቸው የነበረውን የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርነት ወደ ማቻር በማዛወር ነው።

የማቻር ቃል አቀባይ ፑክ ቦቱስ ባሉንግን "የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ መቀየያር የተደረሰውን ስምምነት የጣሰና በአንድ ወገን በተናጠል የተወሰደ እርምጃ ነው" ብለዋል።

የደቡብ ሱዳን ፖለቲከኞች አለመግባባት ሀገሪቱን በድጋሚ ወደ ቀውስ እንዳያስገባት ስጋት ፈጥሯል፡፡

በቅርቡ ሀገሪቱን የጎበኙት ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንሲስ የደቡብ ሱዳን መሪዎች ካለፈው ትምህርት ወስደው ሰላም እንዲፈጥሩ ማሳሰባቸው ይታወሳል፡፡

የ86 ዓመቱ አባ ፍራንሲስ ዓርብ እለት በጁባ በሚገኘው ፕሬዝዳንታዊ ቤተ መንግስት ባደረጉት ንግግር "የሰላምና እርቅ ሂደት አዲስ ጅምርን ይፈልጋል" ሲሉ በአዲሲቷ ሀገር ግጭትን ለማስቆም የተጠናከረ ጥረት እንዲደረግ ጠይቀዋል።

አባ ፍራንሲስ ለደቡብ ሱዳን ፖለቲከኞች ባቀርቡት ተማጽኖም "ከእንግዲህ ወዲህ ደም መፋሰስ፣ ግጭት፣ ሁከትና የእርስ በርስ መገዳደል የለም፣ ከአሁን በኋላ ሕዝቦቻችሁ የሰላም ጥማት አይኑርባቸው" ብለዋል፡፡



## ኢራቅ የአልኮል ሽያጭ መከልከሏን ክርስቲያን ፖለቲከኞች ተቃወሙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በኢራቅ የአልኮል መጠጥ ሽያጭ እና ወደ አገር ውስጥ ማስገባት መከልከሉ ዴሞክራሲያዊ አይደለም ሲሉ የክርስቲያን ፖለቲካ ፓርቲዎች ተቃወሙ።

ኢራቅ ከአንድ ወር በፊት የአልኮል መጠጥን ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ በአገር ውስጥ ማምረት እና መሸጥ የሚከለክል ሕግ አውጥታ የነበረ ሲሆን የአገሪቱ ገቢዎች ባለስልጣን ሕጉን ከትናንት የካቲት እሁድ 26/2015 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚ ማድረግ ጀምረዋል።

ይሁን እንጂ በአገሪቱ ፓርላማ አምስት መቀመጫዎች ያላቸው ክርስቲያን ፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ ውሳኔውን ለመቀልበስ ጥረት እያደረጉ ሲሆን በአብዛኛው የሙስሊም አገር በሆነችው ኢራቅ አልኮል መጠቀም በማሕብረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የለውም፤ ይሁን እንጂ ሰዎች ፍቃድ ካላቸው መጠጥ ቤቶች በይፋ አልኮል መግዛት ይችሉ ነበር።

እአአ 2016 በአገሪቱ ፓርላማ ጸድቆ የነበረ ሕግ የአልኮል መጠጥ ሽያጭ፣ ምርት እና ወደ አገር ማስገባትን ይከለክል ነበር። ይህ ሕግ ከወጣ ከዓመታት በኋላ ተፈጻሚ መሆን እንደሚጀምር የታወቀው ሕጉ በጋዜጣ ከታተመ በኋላ ነው።

ሕጉ ምን ያክል በጥብቅ ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው ግልጽ ባይሆንም በሕጉ መሠረት አልኮል ወደ አገር ያስገባ፣ ያመረተ ወይም የሸጠ እስከ 15ሺህ የእንግሊዝ ፓወንድ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይጠብቀዋል።

ባብሎን ሙቭመንት የተባለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብስብ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሕጉ የአነሳዎችን መብት እና ነጻነት የሚጋፋ በመሆኑ ሕገ-መንግሥታዊ አይደለም ብለዋል። ይህ ሕግ የአልኮል ሽያጭ በጥቁር ገበያው እንዲደራ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል ስጋትን ፈጥሯል።

# ነፃ ሃሳብ

# ዓድዋን ማባከናችን የሚቆጨን...

ከገጽ 5 የዞረ

ብሎ የተመዘገበው አንፀባራቂው የዓድዋ ድል ነው። የድሉ ውጤት ኢትዮጵያ በመላው ዓለም እንድትታወቅ ስላደረጋት ፋሺስት ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመው ወረራ ኢፍትሐዊና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የጣሰ ተግባር እንደሆነ የሚሰብኩ ድምፆች በመላው ዓለም ተስተጋብተዋል። የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም ለሚገኙ ጭቁኖች ያበረከተው አስተዋፅኦ በቀላሉ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም።

እስቲ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱትን የዓድዋ ድል ያስገኛቸውን በጎ ውጤቶች (መልካም አጋጣሚዎች) ይዘን፣ ‹‹ድሉ ያስገኛቸውን ትሩፋቶች በሚገባ መንዝረን ተጠቅመንባቸዋል? በድሉ የተገኙ ውጤቶችን በማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች የበለፀገችና ጠንካራ የሆነች አገርን ለመገንባትስ ተጠቅመንባቸዋል?›› የሚለውን ጥያቄ እንፈትሸው።

የዓድዋ ድል ውጤቶችን እያሰብን የኢትዮጵያን ያለፉትን ዓመታት (በተለይ 50 ዓመታት) ጉዞ ስንቃኝ ‹‹ለመሆኑ ኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያንና የዓድዋ ድል ይተዋወቃሉ?›› ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን። አገሪቱ በድህነት፣ በግጭት፣ በጽንፈኝነትና በጦርነት ጎዳናዎች ላይ ደጋግማ የመመላለሷ አሳዛኝ እውነት፣ የዓድዋ ድል ያስገኘላትን በረከቶች መዘንጋቷንና አለመጠቀሟን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ብዙ ሰው ‹‹ … የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ጥቁሩ የኢትዮጵያ ሰራዊት ነጩን የኢጣሊያ ሰራዊት ድል አድርጎ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ከመገዛት ነፃ አወጣት፤ … ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ብቸኛ አገር ሆነች፤ … አባቶቻችን በከፈሉት ታላቅ መስዋዕትነት ተከብረን ኖርን፤ …›› በማለት የዓድዋ ድል አልፋና ኦሜጋ ትርጉም አገርን ከወራሪ ኃይል መጠበቅ ብቻ እንደሆነና ከዚህ የተሻገረ ዓላማ እንዳልነበረው አድርጎ ያወራል/ይፅፋል። እውነታው ግን የዓድዋ ድል አገርን ከጠላት ወረራ ከመጠበቅ ያለፈ ዓላማና ትርጉም አለው።

በእርግጥ የዓድዋ ድል ኢትዮጵያን ከወራሪ ኃይል ጠብቆ የማቆየት አኩሪ ታሪክ መሆኑ ባይካድም፣ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ከወራሪው የኢጣሊያ ጦር ጋር የተፋለሙት ኢትዮጵያን ከወቅቱ ወራሪ ኃይል ለመጠበቅ (ዳር ድንበሯን ለማስከበር) ብቻ ሳይሆን፣ ወራሪው ኃይል ውሎ አድሮ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰውን ጥፋት በመገንዘብ ያን ጥፋት በእንጭጩ ለመቅጨት ጭምር እንደሆነ መዘንጋትም አይገባም።

ስለዚህ የዓድዋ ድል የመጀመሪያው ውጤት (አበርክቶ) ኢትዮጵያን ከወራሪ ኃይል ጠብቆ ማቆየት ሲሆን ዘላቂው ውጤት ደግሞ ድሉ ያስገኘውን መልካም ፍሬ መንዝሮ ማኅበረሰባዊ ንቃት ያዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ልዩነቶችን አስማምታ አንድነቷን የጠበቀች በአጠቃላይ ኃያል የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠርና መገንባት ነበር። ይህን ዘላቂ ውጤት ማሳካት የነበረባቸው ደግሞ ድሉን ካስገኘው ትውልድ ቀጥሎ የመጡት ትውልዶች ነበሩ። በሚያሳዝንና ሁኔታ እነዚህ ትውልዶች ግን ያን ማድረግ አልቻሉም/አልቻልንም። ለዚህ ቀላሉ ማረጋገጫ ደግሞ ኢትዮጵያ ባለፉት 50 (በተለይ 30) ዓመታት ያሳለፈችበት ሁኔታ ነው።

የዓድዋ ድል ምን ማለት እንደሆነ በቀላል ምሳሌ በማስደገፍ እንመልከት። ዚምባብዌና ደቡብ አፍሪካ፣ በተለይ ከመሬትና ሌሎች ሀብቶች ባለቤትነት ጋር በተያያዘ፣ ቅኝ ግዛት ካመጣባቸው ጣጣ ዛሬም ድረስ ሊላቀቁ አልቻሉም። የዚምባብዌው ሮበርት ሙጋቤ

**የዓድዋ ድል በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ መስኮች ጠንካራና ኃያል አገር ለመገንባት የሚያስችል እምቅ አቅም ያለው ድል መሆኑን መረዳትና መቀበል ያስፈልጋል፡፡ የዓድዋን ድል ያስገኘልንን በረከቶች አውቆ እየመነዘሩ መጠቀምና ማኅበረሰባዊ ንቃት ያዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ልዩነቶችን አስማምታ አንድነቷን የጠበቀች ኃያል ኢትዮጵያን መፍጠር (መገንባት) የድሉን ትርጉም የማወቅ ንቃት ነው፡፡ ይህን በመተግበር ኢትዮጵያን ለታላቁ የዓድዋ ድል የምትመጥን ታላቅ አገር ማድረግ ይገባል!**

መሬትን ከቅኝ ገዢዎቹ ነጮች ነጥቀው ለጥቁሮች መስጠታቸው አገሪቱ ዛሬም ድረስ ልትወጣው ያልቻለችው ከባድ የማዕቀብ አዘቅት ውስጥ ከቷታል። ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ጊዜ እየጠበቀ በሚያገረሽ የመጤ ጠል (Xenophobia) እሳቤ እየተፈተነች ነው።

በአንፃሩ የኢትዮጵያው ሌተናል ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ግን መሬትን የመንግስት የሚያደርገውን አዋጅ ለማወጅ ሲነሱ የገጠማቸው ያደረ የቅኝ ግዛት ጥያቄ/ጫና አልነበረም። [እዚህ ላይ ከታሪክ ጋር ሆድና ጀርባ የሆኑ ጥቂት ጥራዝ ነጠቆች ኢትዮጵያውያን ባላባቶችንና የመሬት ከበርቴዎችን እንደቅኝ ገዢ የመቁጠራቸው አስቂኝ ጨኸት ከተረትነትና ከቀልድ ያለፈ ትርጉም እንደሌለው ማስታወስ ያስፈልጋል።] ይህም አዋጁን በቀላሉ ለማወጅና ለመተግበር ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸዋል። ዓድዋ ማለት እንዲህ ነው/ነበር!

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ነፃነት፣ ክብርና አንድነት ሲሉ በዓድዋና በሌሎች ስፍራዎች ለማመን የሚከብዱ ከባድ ተጋድሎዎችን አድርገው ነፃ አገር ለ‹‹ተተኪው ትውልድ›› ቢያስረክቡም፣ ‹‹ተተኪው በተለይ የአሁኑ ትውልድ›› (በተለይ ልኂቃኑ) ያን ታሪክ ማወቅ አልፈለገም፤ ይባስ ብሎ በብሔርና በሃይማኖት ተከፋፍሎ አገር ለማፍረስ ታጥቆ ሲሰራ ኖረ /አሁንም ይህንኑ የሚሰሩ ግለሰቦችና ቡድኖች አሉ/… ። በዚህም የሰማዕታቱ መስዋእትነት ባከነ፤ ተረሳ።

ታላቁ የዓድዋ ድልም የዚህ አሳዛኝ እጣ ፈንታ ሰለባ ከመሆን አልዳነም። አሁን መጠነኛ መሻሻል ቢያሳይም፣ ‹‹ድሉ የእኛ ብቻ ነው … ድሉ የእነርሱ ነው፤ እኛን አይመለከተንም፤ … እገሌ ለድሉ አስተዋፅዖ አልነበረውም … ›› የሚሉ ረብ የለሽ ጭቅጭቆች በተደጋጋሚ ተደምጠዋል።

ኢትዮጵያ በዘር፣ በሃይማኖትና በአመለካከት ሳይከፋፈሉ ዓድዋ ላይ ጠላትን ድል ያደረጉ ልጆች እናት መሆኗን ማሰብና ከዓድዋ ድል በኋላ ባፈራቻቸው ‹‹ልጆቿ›› ምክንያት በአስከፊ የጽንፈኝነት ፖለቲካ ስትታመስ መመልከት እጅግ አሳዛኝና አስገራሚ ተቃርኖ ነው።

በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሰሞን ‹‹ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ድል … ጀግኖች አባቶቻችንና እናቶቻችን … በቅኝ ግዛት አልተገዛንም … ›› የሚሉ ገለፃዎችን መስማት የተለመደ ነው፤ አሁንም እየሰማን ያለነው ይህንኑ ነው። መገናኛ ብዙኃን ትኩረታቸው በእነዚህ ገለፃዎች የታጀቡ ዜናዎችና ዝግጅቶች ላይ ይሆናል። ይልቅስ በመገናኛ ብዙኃን መነገርና መፃፍ ያለበት ‹‹ከዓድዋ ድል በኋላ የነበሩት ትውልዶች፣ በተለይ የአሁኑ ትውልድ፣ የዓድዋ ድል በረከቶችን ተጠቅሞ ብሄር ግጭና ከልመና የተፋታች ኃያል አገር መገንባት ያልቻለው ለምንድን ነው? የአያት-ቅድመ አያቶቹን ውለታ የበላበት ምክንያትስ ምን ይሆን?›› የሚሉት ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው።

የዓድዋ ድል ያስገኘልንን በረከቶች መንዝረን ተጠቅመንባቸው ቢሆን ኖሮ … ዛሬ በዓባይ ወንዛችን ላይ በምንገነባው ግድባችን ምክንያት ‹‹ጥቅሜ ተነካ›› የሚሉ አካላትና የእነርሱ ወዳጆች ጫና ሊያደርጉብን እንዲሁም ታሪካዊና ሕጋዊ መብታችንን በአደባባይ ሊነጥቁን አይሞክሩም ነበር። [በነገራችን ላይ የዓድዋ ድል በዓባይ ወንዛችን ላይ እየገነባነው እንዳለው ዓይነት ግዙፍ የልማት ስራዎችን እንድንሰራ ስንቅ የሆነ ድል ነበር] … የዓድዋን በረከቶች ብናውቃቸውና ብንጠቀምባቸው ኖሮ በጽንፈኝነት ፖለቲካ የምትታመስ፣ ሚሊዮኖች በችግር የሚሰቃዩባትና የሚፈናቀሉባት …. አገር አትኖረንም ነበር! ለመሆኑ ዓድዋን ማባከናችን የሚቆጨን መቼ ነው?

በየዓመቱ የካቲት 23 በመጣ ቁጥር ስለዓድዋ ድል የተቀነቀኑ ዘፈኖችን እንሰማለን። በቴሌቪዥንና በሬዲዮ የዓድዋን ተራሮች ደጋግመን ማየት እንዲሁም የዳግማዊ አፄ ምኒልክንና የጦር አበጋዞቻቸውን ጀግነት መስማትም ለምደናል። ነገር ግን የቀደምት አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ታሪክ ከመስማት ባለፈ፣ ‹‹ታሪካቸውን ለበጎ ተጠቅመንበታል?›› ብሎ ራስን መጠየቅ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ ‹‹ይህ ትወልድ ለታላቁ የዓድዋ ድል ይመጥናል?›› ተብሎ ሊጠየቅና ሊመረመር ይገባል።

በየዓመቱ የካቲት 23 ሲደርስ ‹‹በአባቶቻችን ጀግንነት እኮራለሁ፤ … ምኒልክ አባቴ፤ ጣይቱ እናቴ … ›› እያሉ ማውራትና መዝፈን ብቻውን ዋጋ የለውም። ቀደምት ኢትዮጵያውያን ባስገኙት ድል መኩራትና ድሉን መዘከር ጥሩ ቢሆንም የድሉን ትሩፋቶች ሳይጠቀሙ፣ ድሀ (ደካማ የሆነች) አገር ይዞ በድሉ ‹‹መኩራት››ና ድሉን ‹‹መዘከር›› ትርጉም የለሽ ድካም ነው። በዓድዋ ለመኩራት ዓድዋን ማወቅና መጠቀም ይገባል!

የዓድዋ ድል በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ መስኮች ጠንካራና ኃያል አገር ለመገንባት የሚያስችል እምቅ አቅም ያለው ድል መሆኑን መረዳትና መቀበል ያስፈልጋል። የዓድዋን ድል ያስገኘልንን በረከቶች አውቆ እየመነዘሩ መጠቀምና ማኅበረሰባዊ ንቃት ያዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ልዩነቶችን አስማምታ አንድነቷን የጠበቀች ኃያል ኢትዮጵያን መፍጠር (መገንባት) የድሉን ትርጉም የማወቅ ንቃት ነው። ይህን በመተግበር ኢትዮጵያን ለታላቁ የዓድዋ ድል የምትመጥን ታላቅ አገር ማድረግ ይገባል!

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር

በየሳምንቱ የሚታተም

# ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በኅብረት ሥራ ማኅበራት

**በዳንኤል አበበ**

ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ከ1400 ዓመት በፊት ጀምሮ የነበረ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ከሳዑዲ አረቢያ ወደ ስፔን፣ ሞሮኮ፣ ህንድ፣ ቻይና እና ሰሜን አሜሪካ ቀስ በቀስ እየተስፋፋ መጥቷል። እ.ኤ.አ በ1963 ዓ.ም. ጀምሮ በአፍሪካ አህጉራችን በግብፅ አገር የሚገኘው ሚት ግራምን የኅብረት ሥራ ማኅበር ዘመናዊ የወለድ አልባ ፋይናንስ አሠራርን በመጀመር ፈር ቀዳጅ ለመሆን በቅቷል። ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በቀላል አገላለጽ ከእምነት ጋር በተያያዘ ምክንያት ወለድ መክፈልም ሆነ መቀበል የሚከለከልበት የአገልግሎት አይነት ነው። ወለድ በሁሉም እምነቶች የተወገዘ ተግባር ነው።

ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ማለት ሰዎች ገንዘባቸው ያለምንም የወለድ ክፍያ በአስተማማኝ ቦታ እንዲቀመጥላቸው እና ከወለድ ውጪ የብድር አገልግሎት ከፋይናንስ ተቋማት የሚያገኙበት የፋይናንስ አገልግሎት አይነት ነው። አገልግሎቱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ወጪዎች እንዲሁም በሥራ ሂደት የሚከሰቱ ትርፍና ኪሳራዎች ሀይማኖታዊ መርሆችን ብሎም በሀይማኖታዊ/በእምነቱ ሥርዓት ውስጥ የተከለከሉ ጉዳዮችን በጥንቃቄ ለይቶ እና ማዕከል አድርጎ የሚስተናገድበት አሰራር ነው። የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎቶችን መቅረፅ፣ በስፋት እንዲሰራበት እና ተደራሽ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረትን፣ የረጅም ጊዜ ስልጠናና ልምድን የሚጠይቅ ነው።

በአሁኑ ወቅት ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በዓለማችን ከ80 በላይ አገራት ውስጥ በስፋት እየተሰራበት የሚገኝ ሲሆን፣ በዩናይትድ ኪንግደም ሙሉ በሙሉ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚሰጡ 22 የፋይናንስ ኅብረት ሥራ ማህበራት ለደንበኞቻቸው ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። የወለድ አልባ የፋይናንስ እና የኅብረት ሥራ አሰራር የሚያመሳስሏቸው የጋራ ዕሴቶች አሏቸው። ኅብረት ሥራ ማህበራት ለዛሬው የወለድ አልባ የባንክ አሰራር መነሻ መሆናቸው ብዙዎች ይስማማሉ።

በአገራችን ኢትዮጵያ ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን የሚፈልግ የኅብረተሰብ ክፍል ቁጥሩ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ አገልግሎቱ እንዲሰጥ በህግ በመፈቀዱ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎቱን መስጠት ጀምረዋል። ከጊዜ ወደ ጊዜም ህብረተሰቡ አገልግሎቱን የመጠቀም ፍላጎት እያደገ በመምጣቱ ምክንያት የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራትም እንደ ፋይናንስ ተቋምነታቸው አገልግሎትን እንዲሰጡ ጥያቄ ከአባላት እየቀረበላቸው ይገኛል። የአገልግሎቱ ፈላጊ ከመጨመሩ ጋር ተያይዞ በአገራችን የሚገኙ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት የወለድ አልባ ፋይናንስ አገልግሎትን ለደንበኞቻቸው በአማራጭነት በማቅረብ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ዕለት በዕለት እያሳደጉ ናቸው። የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት ለዚህ አማራጭ የፋይናንስ አገልግሎት ተወዳዳሪ ለመሆን በዋነኛነት አደራጃጀታቸውን፣ የአሰራር ሥርዓታቸውን፣ የሰው ኃይላቸውን እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸውን በማዘመን ሂደት ተግባራት ላይ ተጠምደዋል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን (ከቀድሞው የፌደራል ኅብረት ስራ ኤጀንሲ ጀምሮ) ወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎትን ለገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበራት አማራጭ የፋይናንስ አገልግሎት እንዲሆን ለማስቻል እና የአባላትን የፋይናንስ ፍላጎት ተደራሽነት ለማሳደግ ትኩረት ሰጥቶ የተለያዩ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል።

ኮሚሽኑ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት አገልግሎቱን በሚፈልጉ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲስፋፋ እንዲሁም አፈፃፀማቸው ያደገ፤ የአባላትን ፍላጎት ያሟሉ እና በፍትሃዊነት ላይ የተመሰረተ ተጠቃሚነትን ያረጋገጡ ብሎም ተወዳዳሪ የሆኑ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የማደራጀት እና የማጠናከር ስራውን ከጀመረ አራት ዓመታት አስቋጥሯል። የቀድሞ የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ (የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን) የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት እንዲስፋፋ በፈር ቀዳጅነት የአሠራር ማንዋሎችን እና መመሪያዎችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው የኅብረት ሥራ አደረጃጀት አካላት ከማድረሱም (ወደ ታች ከማውረዱም) ባሻገር አገልግሎቱን በትክክል ለመተግበር ለሚመለከታቸው አካላት አቅም ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ስልጠናዎችን ሰጥቷል። በመስጠትም ላይ ይገኛል።

ምንም እንኳን በአገራችን የኅብረት ሥራ አጀማመር ከስድሳ (60) ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት ውስጥ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።

ይህ አገልግሎት በአገራችን በገንዘብ ቁጠባና ኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀት ወስጥ እንደ አገልግሎት ከተካተተ ጀምሮ በቀድሞው የፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ (የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን) አማካኝነት በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል። አገልግሎቱ እንዲስፋፋ አገልግሎቱ ከተጀመረባቸው የአገራችን አካባቢዎች የተጀማመሩ አተገባበሮች በመቀመር ምርጥ ተሞክሮዎችን አገልግሎቱን ወደ አልጀመሩ እና አገልግሎቱን ለመጠቀም ለሚሹ የአገራችን ክፍሎች ለማዳረስ እና ለማስፋፋት በርካታ ስራዎች ተከውነዋል። እየተከናወኑም ይገኛሉ።

በዚህ የአገልግሎት ማዕቀፍ ውስጥ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አመራር አካላት እና የዘርፉ ባለሙያዎች በወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት አተገባበር ላይ ያለባቸውን ውስንነት በመቅረፍ ትኩረት እንዲሰጡ እንዲሁም በሁሉም የአገራችን አራቱም ማዕዘናት በሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት በአባላት ፍላጎት ላይ በተመሰረተ የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት ተግባራዊ እንዲያደርጉ አበረታች ስራዎች ተከናውነዋል።

በመሆኑም ፍላጎት ተኳር የሆነው የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት በሚጠበቅ ደረጃና ጥራት በሌሎች የአገራችን አራቱም ማዕዘናት እንዲሰፉ እና ተደራሽ ለማድረግ በዋናነት የኅብረት ሥራ ዘርፍ አመራሮች፣ ባለሙያዎች ብሎም ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው እና አቅማቸውን አስተባብረው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል።

አድራሻ | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Ethiopia cooperative Commission | Website: www.fca.gov.et






በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ